# ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስና በ1842 ዓ.ም. በእንግሊዝና በኢትዮጵያ መካከል በተደረገው ውል የተቋቋመው ግዛት ለቀቅ ልዩ የዳኝነት ሥልጣን

ታምሩ ወንድምአገኘሁ *

## መግቢያ

ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ስማቸው በውደሳ ገኖ የተነሳውን ያህል በጥላቻም ከተወሱ መሪዎች መካከል አንዱ ሳይሆኑ አይቀሩም ። በእርግጥም ሊወደሱበት ከሚገባቸው ሥራዎች አንዱ በራስ ዓሊ ላይ በተጐናጸፉት ድል ተማካይነት ከሥልጣነ መንግሥቱ ጋር የተረከቡትን ለእንግሊዝ ቆንስል ልዩ የዳኝነት ሥልጣን የሚሰጠውን ውል አልቀበልም ማለታቸው ነው ** ። በቀላል አገላለጽ ከግዛት ውጭ ልዩ የዳኝነት ሥልጣን የሚያጐናጽፈው የውል መብት ባዕዳን ከራሳቸው ግዛት ውጭ እንኳ ሲገኙ በራሳቸው ብሔራዊ ሕግጋት ጥበቃ ሥር እንዲኖሩ ዋስትና የሚሰጥ ሥርዓት ነበር ።

ይህ ይሆንበት የነበረው ምክንያቱ ከዘመን ዘመን እየተለያየ የመጣ ነው ፤ በመጀመሪያ መሰረቱ የሃይማኖት ልዩነት ሲሆን ፤ ከጊዜ በኋላ ግን እንደ ንግድ የመሳሰሉትን ሌሎች ጥቅሞችን መጠበቂያ ሰበቦች ማካተት ጀመረ ። በጽንሰ ሃሳቡ አራማጆች አባባል ይህ የተለየ ጥበቃ ያስፈለገው ኋላ ቀርና ዝቅተኛ የሆነ የዕድገት ደረጃ ያላቸው ተቀባይ አገሮች የውጭ ዜጐችን አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ለመጠበቅ ሥልጣኔ የሚጠይቀውን ሥርዓት የሚያሟላ የሕግ መድረኮች ስለሌላቸው ነው ። [1]

ግዛት ለቀቅ ልዩ የዳኝነት ሥልጣን በዚህ መልኩ በአጠቃላይ ባንድ በኩል የሰለጠነ ተብሎ የሚጠራ መንግሥትና በሌላ በኩል ደግሞ ኋላቀር የሆነ መንግሥትን የሚያቅፍ ስምምነት ሆነ ። ነገር ግን በዚህ ዓይነት ውል ውስጥ ኋላቀር የሆነው ተዋዋዩ መንግሥትን ያለ ምንም ጥቅም ከነጻዊ የላቀ መብቱ ላይ ቀንሶ መስጠት ይጠበቅበት ስለነበረ ምንግዜም ቢሆን ተጐጂ እንጂ ተጠቃሚ አልነበረም ።

ይባስ ነገር ደግሞ ይህን ዓይነት ስምምነት ከአንድ መንግሥት ጋር ሲደረግ የውሉ ተዋዋይ ያልሆኑ ሌሎች ነገሮች የውሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችል ነበር ። ይህ የሚሆነው ቀድሞ በነበሩ ወይም አዲስ በተፈረሙ ውሎች ውስጥ የሚገኘውን " ይበልጥ ተጠቃሚ አገር " የሚለውን አንቀጽ ሥራ ላይ በማዋል ነበር ። [2] ይህ ዓይነቱ አሠራር በግልጽ እንደሚታየው የውል ተቀባዩን መንግሥት ራሱን በራሱ በነጻ ማስተዳደሩን በብዙ መንገድ የሚገድብ ነበር ። ይህን በተለያዩ ሁኔታዎች ስናየው ባዕዳኑን ሕብረተሰብ ከሚኖሩበት ወይም ከሚሰሩበት መንግሥት የሥልጣን ክልል ውጭ ማድረግ ነበር ። በተጨማሪም ስምምነቱ ቆንሲሉን ወይም የዲፕሎማቲክ ልዑክ የሆነውን የውጭ አገር ሰው የተቀባዩን መንግሥት የዳኝነት ሥልጣን እንዲነጥቅ ብቻ ሳይሆን የራሱንም አገር የሕግ ሥር

** ከዚህ መጣጥፍ ቀጥሎ የሚገኙትን የቴዎድሮስን ደብዳቤዎችና የ1842 ዓ.ም የወዳጅነትና የንግድ ውል እንደ ማስረጃ ሰነድ ስለሚጠቀሙ ተመልከት (አዘጋጅ) ።

ዐት ቢያንስ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ሉዐላዊና ነጻ በሆነ አገር ውስጥ ሥራ ላይ እን ዲያውል አስችሎታል ።

የንግድ የሥራ ዘርፉ በብዛት የሚንቀሳቀሰው በውጭ አገር ተወላጆች ስለ ነበረ ይህ ዓይነቱ ስምምነት ይህን የሥራ ዘርፍ ከተቀባዩ መንግሥት ቁጥጥር ውጭ እንዲሆን የማድረግም ተጨማሪ ውጤት አለው ። ይህም በአጭሩ ተቀባ ዩን መንግሥት ለባሰ ጉዳት የዳረገና ብዙ ጊዜም ወደቅኝ ግዛትነት ወይም በሞ ግዚትነት ወደ መተዳደሩ ደረጃ ዝቅ እንዲል ሁኔታዎችን ያመቻቸ የጥቃት በር ከፋች ነበር ።[3]

የዚህ ዓይነቱን አሠራር መሠሪ ባህሪይ ያልተረዱት ሁሉም ለሰለባው የተ ጋለጡ መንግሥታት መሪዎች አልነበሩም ፤ ከ1847 — 1860 ዓ.ም. የነገሡት ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የዚህ ዓይነቱን ውል እኩይ ነት አስቀድመው ከተገነዘቡትና ፊት ለፊት ለመቋቋም ከቆረጡት መሪዎች አንዱ ነበሩ ። በኢትዮጵያ ነጻነት ላይ ይህን የመሰለ ማዕቀብ ለመጣል የተደረ ገው ሙከራ በዓይነቱ ቀዳሚና የመጀመሪያው ነው ። ቴዎድሮስ ያሳዩት ሃሳበ ጽኑነት የእንግሊዝ ሥልጣነ መንግስት በኢትዮጵያ እንዲንሰራፋ ከመቀበል ይልቅ የራስን ሕይወት በገዛ እጅ ማጥፋትን የተሻለ ምርጫ አድርጎ እስከማቅ ረብ የዘለቀ ነበር ።

## የ1842 ዓ.ም. ውል መነሻ

ይህ አነስተኛ ጽሑፍ የውሉንም ሆነ የአጼ ቴዎድሮስን ታሪክ ለማቅረብ አይሞክርም ። በዚህ ጽሑፍ ለማድረግ የታቀደው በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መካ ከል በ1842 ዓ.ም. በተደረገው ውል ውስጥ ስላለው የቆንሲል ልዩ የዳኝነት ሥል ጣን ዋና ዋና ነጥቦችን ለመጠቋቆምና በንጉሠ ነገሥቱ ከተሰነዘሩት ተቃውሞ ዎች መካከል ጥቂቶቹን ለማመልከት ነው ።

ሆኖም ግን ይህን ለማድረግ በመጀመሪያ የውሉን መነሻና ከሱም ጋር በቅ ርብ የተያያዙ ሰዎችን ታሪክ በጥቂቱም ቢሆን መዳሰስ ተገቢነት ይኖረዋል ።

በአንድ መልኩ የ1842 የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ውል ታሪክ የዋልተር ቺችል ፕላውዴን ታሪክ ነው ለማለት ይቻላል ። ዋልተር ፕላውዴን እንደ አው ሮፓውያን አቆጣጠር ነሐሴ 3፥1820 ተወለደ። በ19 ዓመቱ ወደ ሕንድ ሄደ ፤ እዛም በካልካታ የሚገኘው የካር ፤ ታጉርና ኩባንያው ድርጅት ሠራተኛ በመሆን ለአራት ዓመታት ከሠራ በኋላ ወደ እንግሊዝ አገር ለመመለስ ከሥራው ተሰናበተ ። በ1836 ገደማ ስዌዝ ከተማ ፣ ግብጽ አገር ፣ እንደደረሰ በብሪታንያ ጦር ውስጥ የቀድሞ የባህር ኃይል መኮንን የነበረውን ሚስተር ጆን ቤልን አገኘውና የነጭ ዓባይን ምንጭ ለማግኘት በሚደረገው ፍለጋ ከሚስተር ቤል ጋር ለመጓዝ ወዲያውኑ ወሰነ ። አምስት ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ ያደረገው ቆይታ በጊዜው ታዋቂነት የነበራቸው መሪዎች ዕውቀትና ከበሬታም አትርፎለት ነበር ።

ከነሱም መሐል ራስ ዓሊና ደጃች ውቤ ይገኙ ነበር ። እነዚህ ሁለት ኃያላን ጦረኞች የወቅቱ ከፍተኛ የሥልጣን ተፋላሚዎች ነበሩ ። የሚፋለሙትም አንዱ ሌላውን በመጣል የእንጋሽነቱን ሥልጣን ይዞ የፈለገውን ለስም ያህል በማንገስ በስሙ ጠቅልሎ አገር ለመግዛት ነበር ።

በዚያ ለሥልጣን በሚደረገው መራኮት ውስጥ ሁኔታዎች ያደሉት ለራስ ዓሊ ነበርና ፣ ፕላውዴን ወደ እንግሊዝ አገር ለመሄድ ሲነሳ እግረ መንገዱንም የራስ

ዓሊ መልዕክተኛ በመሆን ለማገልገል ተስማማ ፡፡ ከፕላውዴን ጋርም ልዩ መልዕክተኛ በመሆን አለቃ ደስታ ተልከው ነበር ፡፡ ነገር ግን በቀይ ባሕር ላይ ሲጓዙ ያጋጠማቸው የመርከብ አደጋ ክፉኛ አስመርሯቸው ነበርና ካይሮ ሲደርሱ ወደ ለንደን ጉዞውን ለመቀጠል ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ ፡፡ [4]

መልዕክቱ እስከዚህም ቁም ነገር ያልነበረው በመሆኑ ራስ ዓሊ በጽሑፍ ከማድረግ ይልቅ በቃል እንዲላክ ነበር የመረጡት ፡፡ ልዩ መልዕክተኛው ወደ እንግሊዝ አገር ጉዞውን ለመቀጠል ፈቃደኛ ባለመሆናቸውና ፤ ለንግሥቲቱ እንዲሰጡ የተላኩትን ጥቂት የስጦታ ዕቃዎች በአደጋው ምክንያት ውሀ ስለበላባቸው የቃል መልዕክቱን ብቻ ለታላቋ ብሪታንያ የማቅረብ ብቸኛ ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ያረፈው ፕላውዴን ላይ ነበር ፡፡

በራስ ዓሊ በኩል የተልዕኮው ዓላማ ከመልካም ምኞት መግለጫነት የሚያልፍ አልነበረም ፡፡ ይህንኑ ከፕላውዴን ማስታወሻ ውስጥ ቀጥሎ ከተጠቀሰው ክፍል መረዳት ይቻላል ፡፡ [5]

> መልካም ምኞት መግለጫዎችን ከመለዋወጥና
> በዚሁ መንፈስ ለእንግሊዝ ተጓዦች ሁኔታዎችን
> የሚያመቻቹና ጥበቃም የሚሰጡ መሆናቸውን ከመግለጥ
> ባሻገር ራስ ዓሊ ዓላማ ኣላቸው ብሎ መገመት አይቻልም ፡፡

ለፕላውዴን ግን ተልዕኮው የታወቀ ዓላማና ውጤት ነበረው ፡፡ ከሁሉ በፊት ተልዕኮው በብሪታንያ መንግሥት ወጪ እንግሊዝ አገር ደርሶ ለመመለስ አስችሎታል ፡፡ ሁለተኛም አጋጣሚው ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር የመገናኘት ዕድሉን ከፍ ስላደረገለት ብሪታንያ ኢትዮጵያን በተመለከተ መከተል ይገባታል ብሎ የሚያምንበትን ሀሳብ ለመሰንዘርና ለተቀባይነቱም የበኩሉን ግፊት ለማድረግ ሳያስችለው እንዳልቀረ ይገመታል ፡፡ በመጨረሻም ገኖ ብቅ ያለው ፕላውዴን የዓሊ መልእክተኛ ሳይሆን ፕላውዴን እንግሊዙ ነበር ፡፡ ታላቋ ብሪታንያም በጉዳዩ ላይ ሳትዘገይ ውሣኔ ሰጠች ፤ በ1840 ዓ.ም. ገደማ መቀመጫው ምጽዋ ላይ ሆኖ በሀበሻ የእንግሊዝ ቆንሲል እንዲሆን ፕላውዴንን ለመሾም ፓልመርስቶን ወሰነ ፡፡

ቀጥሎም ተጨማሪ ምክር ተደርጎ የሥራውን ዝርዝርና መመሪያ ከተቀበለ በኋላ ለራስ ዓሊ እንዲያደርስ የተሰጠውን ደብዳቤና " መሰረታዊ ለውጥ ሳይደረግበት " እንዲፈራረሙ የተረቀቀውን ውል ይዞ በምጽዋ በኩል አድርጎ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት በጥር 1841 ዓ.ም. ጉዞውን ጀመረ ፡፡ እንግዲህ የፕላውዴን ተልዕኮ ሁለት ተግባሮችን ማከናወን ነበር ፡፡

የመጀመሪያው በምጽዋ የእንግሊዝን የቆንሲል መሥሪያ ቤት ማቋቋምና መቀመጫው እዚያ ሆኖ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የብሪታንያ ቆንስል በመሆን ማገልገል ፣ ሁለተኛው ደግሞ በንጉሡ ወይም በንጉሡና በራስ ዓሊ ስም የተረቀቀውን ውል ራስ ዓሊ እንዲስ ማሙበትና ሁለቱም እንዲፈርሙበት ማድረግ ነበር ፡፡ [6] ይህ የፕላውዴን ጥንድ ተልዕኮ ውጤትንም ውድቀትንም የተላበሰ ነበር ፡፡ ራስ ዓሊን በሚመለከት ተልዕኮው የተሳካለት ሲሆን በአጼ ቴዎድሮስ በኩል ግን ያጋጠመው ተልዕኮውን ሙሉ በሙሉ የሚያከሽፍ ሁኔታ ነበር ፡፡

የቆንስላው መቋቋምና የቆንሲሉ መሾም ከሁለቱ አገሮች የጋራ ስምምነት ያልመነጨ በመሆኑ የታላቋ ብሪታንያ ብቸኛ ሃሳብ መሆኑ ግልጽ ነው ፡፡ ሆኖም ቆንሲሉ ሥራውን እንዲያካሂድ የታሰበውን መሥሪያ ቤት በወቅቱ በቱርክ አስ

ተዳደር ሥር በምትገኘው በምጽዋ አድርጎ መሆኑ ይህን የእንግሊዝ ብቸኛ ውሣኔ ውጤት የሚያለሳልሰው ይሆናል ።

ምንም እንኳ ፕላውዴን የመጀመሪያው ቆንሲል ሆኖ ቢሾምም ለሀበሻ አገር ቆንስላ የማስፈለጉን ሃሳብ ለማፍለቅ የመጀመሪያው ሰው አልነበረም ። ቻርልስ ቤክ ቀደም ብሎ በ1838 ዓ.ም. ይህን ሃሳብ ማቅረቡን ገልጧል ። ስለዚህም ሲጽፍ "የነገሩ መነሻ የእርሻ ሠራተኞችን ከሀበሻ አገር ለማግኘት በ1838 ዓ.ም. የአቀረብኩት ሃሳብ እንጂ ከፖለቲካ ዓላማ የመነጨ አልነበረም " ብሏል ።[7] ፓልመርስቶን ምክንያቱን ከንግድ ጋር ያያይዘዋል ፤ ፕላውዴንም ቆንስላው በኢትዮጵያ ምድር ላይ መቋቋም አለበት በማለት አጠንክሮ ቢያሳስብም ፓርልመርስቶን "እኛ የምንፈልገው ንግድ ነው ፤ ለንግድ ደግሞ መሬት ነ ያስፈልገውም "[8] በማለት ሃሳቡን ውድቅ አድርጐታል ።

ነገር ግን ቆንስላውን ማቋቋም ያስፈለገበት ምክንያት ወይም ለቆንስሉ የተመደቡት ሥራዎች በቤክና በፓልመርስቶን እንደተባለው ፖለቲካ ነክ ያልሆኑ ወይም ቀላል ዓላማ ያላቸው ፈጽሞ አይመስሉም ። ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ የተከሰቱት ሁኔታዎች በግልጽ የሚያስረዱት ይህንኑ ነው ። በሸዋ ፣ በትግራይና በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ መሳፍንቶችን ድጋፍ ለማግኘት ሃይማኖትንና ፖለቲካን መሣሪያ በማድረግ በተለይም እንግሊዝና ፈረንሳይ ያጧጡፉት በነበረው ትግል የተንጸባረቀው በአውሮፓውያን መካከል በወቅቱ የተካሄደው ርኩቻ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረጉ ግልጥ ነው ።

ፈረንሳይ በአካባቢው ለመስፋፋት ያላትን አዝማሚያ ተገንዝቦ እንግሊዝ ከዚህ አደጋ ራሷን ለመከላከል እንድትችል እንግሊዛዊው ቪስካውንት ቫሌንሺያ (የቀድሞ ሰር ጆርጅ አንስሌይ) ሥጋቱን ገና በ1797 የገለጸው በሚከተለው አኳኋን ነበር ።[9]

"የእስልምና ግማሽ ጨረቃ ካሁን በኋላ ለክርስትና አደገኛነት የለውም ፤ ነገር ግን ከሱ ያላነሱ አደገኛነት ያላቸው በማንሰራራት ላይ ያለችው የፈረንሳይ ንስር በጥንታዊ ተቋሞች ላይ ጠቅላላ ውድመትን ለማስከተል በማስፈራራት ላይ ነው ፡ ግፈኛ ጌታቸውም እቅዱን ያወጣው በተለይ በምስራቃዊው የእንግሊዝ ግዛት ላይ መሆኑ ግልጽ ነው ። ግብጽም የተያዘችው ይህን ዓላማ ለማራመድ ሲባል ነው ፤ ይህም የአረብ ኃይሎችን ወዳጅነት ለማሳደግ የሚደረግ ጥረት ነው ። ሀበሻ ከነዚሁ ሁሉ የላቀ ጠቀሜታ ያላት ቢሆንም እንደ እድል ሆኖ ወደ ሀበሻ ዘልቆ ለመግባት የሚቻል መሆኑን ለፈረንሳይ እስካሁን አልተከሰተላትም ። "

ቪስካውንቱ ታላቋ ብሪታንያ በሀበሻ ምድር ቀድማ የደረሰች እንደመሆኗ በዚህ ዕድሏ ተጠቅማ ከአገሪቱ ጋር ግንኙነት እንድትመሠርትና " ፈረንሣይ ምንጊዜም ቢሆን እንዳትገባ እንድታደርግ ፤ ግን በዚህ አጋጣሚ ሳንጠቀም ችላ ብንል የድክመታችን ተጠቃሚዎች ፈረንሣዮች ይሆናሉ " ሲል አስገንዝቧል ።

በ1832 ዓ.ም. ብሪታንያ ኤደንን መያዝዋና የካቶሊክ ሚሲዮንም በሰሜናዊ ኢትዮጵያ መስግሰግ እንዲሁም በዘይላና በታጁራ ፈረንሣዮች በወቅቱ ያደርጉት የነበረው ከፍተኛ እንቅስቃሴ በሁለቱ አገሮች መካከል የሚካሄደውን ሽኩቻ ለማሻሻል የሚረዱ ምልክቶች አልነበሩም ።

ፕላውዴን ከሞተ በኋላ ኃላፊነቱን አልተወጣም ተብሎ ከውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤታቸው ባለሥልጣኖች ለተሰነዘረበት ወቀሳ የፕላውዴን ወንድም ከሰጠው ምሬት የተሞላበት መልስ የምንረዳው ይህንኑ ሁኔታ ነው ። እንደሱ

ሊባባልም [10] " የቆንሲሉ ኃላፊነቶች የውጭ ኃይሎችን ፤ በተለይ የፈረንሳይን ፣ ተንኮል በተጠንቀቅ መጠበቅና ጎጂነቱን መመለስ ፤ በሀበሻና በግብጽ መሐል ሰላምን መጠበቅ ፤ ባርነት እንዲወገድ ማስደረግና በታላቋ ብሪታንያና በሀበሻ መሐል የንግድ ልውውጥን መመስረትና ማራመድ ናቸው ። "

ለማንኛውም የቆንሲል መላኩ ዓላማ ምንም ሆነ ምን ፕላውዴን እንደቀድሞው በተራ ተጓዥነቱ ሳይሆን የታወቀ ተልዕኮ ያለው የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ሆኖ በ1841 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ተመልሶ ጉንደር ገባ ።

ለውጭ ጉዳይ መ/ቤት ፕላውዴን ያቀረበው ሪፖርት እንደጠቆመው ለራስ ዓሊ ያመጣውን ስጦታዎች ለማበርከትም ሆነ ለብሪታንያ ቆንስላነቱ ተቀባይነት ለማግኘት ያጋጠመው ችግር አልነበረም ።

እንዲሁም የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ብቻውን ያረቀቀውን ውል ይዘት በተመለከተም ያጋጠመው ምንም ዓይነት ተቃውሞ አልነበረም ።

ከውሉ ጋር የተያያዘ አንድ ችግር ቢኖር የውሉን መንፈስና ይዘት ለመግለጥ እሳቸውን አግኝቶ ለመነጋገር ጎለመቻሉ ነበር ። ፕላውዴን እንደገለጠው በዚህ ረገድ ጆን ቤል የሚባለው የአገሩ ሰው በጣም ረድቶታል ፤ ጆን ቤል ቀደም ብሎ ለራስ ዓሊ አድሮ ስለነበር በርሳቸው ዘንድ ከፍተኛ ክብርና ሞገስ ማግኘት ችሎ ነበር ።

በመጨረሻም ፕላውዴን ለስምንት ወራት ከራስ ዓሊ ጋር ዘመቻ ሲንከራተት ከቆየ በኋላ በጉጃም ክፍለ ሀገር እናውጋ በምትባል ሥፍራ ጥቅምት 24 ቀን 1842 ዓ.ም. የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤቱ እንዳዘዘው ንጉሡን ሳይሆን ፤ ራስ ዓሊን ውሉን ለማስፈረም ችሏል ።

በዚህም የተነሳ ራስ ዓሊ " የፈረሙት ውል ከፍተኛ ቁምነገር ያዘለ መሆኑን እንዲገነዘቡት ለማድረግ ይረዳ ዘንድ " የውሉ ማጽደቂያ ሰነድ ለራስ ዓሊ እንዲላክ ፕላውዴን ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ያቀረበውን ማሳሰቢያ መሥሪያ ቤቱ ተቀብሎት የተላከላቸውን የማጽደቂያ ሰነድ ራስ ዓሊ የካቲት 22 ቀን 1844 ዓ.ም. ተቀብለውታል ። [11]

ውሉ የተፈረመበትን ሁኔታ ፕላውዴን ስዕላዊ በሆነ አገላለጽ እንደሚከተለው አስቀምጦታል ። [12]

> . . . አንድ ቀን ጠዋት ወደ ዕልፍኝ ድንኳን ገባሁና ጸሐፊዎ ውሉን እንዲያነብላቸው አደረግሁ ።
> . . . . . ወዳጃቸው ከሆነ አንድ ሹም ጋር በድንኳኑ ውስጥ ስለ ታሰረ አንድ ፈረስ ይነጋገሩ ነበር ። ፈረሱ የታሰረው አጠገቤ ነበርና ደጋግሞ ሊረግጠኝ ምንም አልቀረውም ። ሁላችንም ፣ ራስም ጭምር የተቀመጥነው መሬት ላይ ነበር ። ቁምነገር የሌለው ጥያቄ አቅርበውልኝ እኔም ይልቁን የሚነበበውን ጉዳይ ልብ ብለው ይከታተሉ ብዬ ተማጸንኩ ። እሳቸውም ሀሳቤን ተቀብለው በሰፊው አዛጉ ። የኔ ማብራሪያና መግለጫ ታክሎበት ሰነዱን ዘለቅነው ፤ ከዛም ሰነዱ በያዘው ነገር ምንም ጉዳት እንዳላዩበት ራስ ተናገሩ ፤ እንዲያውም በተቃራኒው እጅግ በጣም ጥሩ ሆኖ እንዳገኙት ከገለጡ በኋላ ሀበሻ በነበረችበት ሁኔታ በአሥር ዓመት እንኳ አንድ እንግሊዛዊ ነጋዴ ሊመጣበት አይችልም

ብለው መገመታቸውንና በዚህም የተነሳ ውሉ ፈጽሞ ጥቅም የለሽ ሆኖ እንደሚቀር እምነታቸውን ገለጡ ። ቀጥሎም በሁለቱ ውል ቅጂዎች በማህተማቸው ካተሙ በኋላ የራሳቸውን ድርሻ ለሚያቀርቡት አንድ ደብተራ ሰጥተው ደብረ ታቦር ወስዶ እንዲቀልፍበት አዘዙ ።

ስለሆነም ዓሊ ሥልጣን ላይ ብዙ የሚቆዩ አልሆኑም ። እንኳንስ የውሉን ሥራ ላይ መዋል ሊያዩ ቀርቶ ቆንስላውንና የውሉን ዋንኛ ነጥቦች በአደባባይ ለማወጅ እንኳ ፋታ አላገኙም ። ወታደሮቻቸው በአማቻቸው ና በኋላ ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በሆኑት በካሣ ጦር በተከታታይ በመሸነፋቸው ውድቀታቸው ውሎ ሳያድር ተፋጥኖ ደረሰ ።

ከአራት ዓመት በፊት " ዓሊ ንጉሠ አበሻ " የሚል ቅጥያ ጨምረው ውሉን የፈረሙት የራስ ዓሊ ሥልጣን በፍጥነት ማሽቆልቆልና የነገሮች መለዋወጥ ፕላውዴንን እጅግ ስላሳሰበው ከራስ ዓሊ ጋር የተደረገው ውል " ዋጋ ቢስ መሆኑ የማይቀር ነው " በማለት ሥጋቱን ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት እስከመግለጽ አድርሶት ነበር ። [13] ወዲያውኑ ራስ ዓሊ ከመድረኩ ሲገለሉ የሳቸውን ቦታ ለመያዝ ካሣና ውቤ ዋንኛ ተፎካካሪዎች ሆነው ብቅ አሉ ። ይህም ሽኩቻ ብዙ የቆየ አልነበረም ።

በካሣና በውቤ ወታደሮች መካከል በየካቲት ወር 1847 ዓ.ም. የተደረገው የደረስጌ ጦርነት የውቤ ዕድልና የዘመነ መሳፍንት ማክተሚያ ሆኗል ። በተከታታይ ውጊያዎች ድል አድራጊነቱን የተጐናጸፉት ካሣ ከሳቸው በፊት የነበሩ መሪዎች ይሰገበገቡለት የነበረው የሺሚ ሻሪነት የውሸት ሥልጣን ሊያረካቸው አልቻለም ። ሁኔታውን ለማስወገድ ቆርጠው የተነሱ በመሆናቸው በስም ብቻ በዙፋን ላይ በተቀመጠው ንጉሥና ሥልጣንን ጠቅልሎ በያዘው አምባ ገነን መካከል ያለውን መጋረጃ አስወግዶ ሁለቱንም በአንድ መሪ ሰውነት ማዋሀድ ነበረባቸው ።

ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተሰኝተው የካቲት 4 1847 ዓ.ም. ገደማ በደረስጌ ማርያም ቤተክርስቲያን ዘውድ ሲደፉ ያሳኩት በትክክል ይህንኑ ነበር ። ያ ወቅትም ያረጀው ዘመን የማክተሚያው መጀመሪያና የአዲሱ ደግሞ የመጀመሪያው ምዕራፍ ነበር ለማለት ይቻላል ።

ካሣ ቴዎድሮስ ተብለው በመንግሥት ሥልጣን ቁንጮ ላይ በመቀመጣቸውና ጦርነቱም ያስከተለውን ሁከት ምክንያት በማድረግ ፕላውዴን ከራስ ዓሊ ጋር ስለተፈራረመው ውልና እራሱም በኢትዮጵያ የብሪታንያ ቆንሲል ስለመሆኑ ለቴዎድሮስ ማስታወስ ወቅቱ መስሎ ታየው ።

በአዲሱ ጌታው ሥር ይበልጥ በተመቸው በጆን ቤል አግባቢነት ሰኔ 1847 ፕላውዴን ቴዎድሮስ ቤተመግሥት ተገኘ ።

## የ1842 ውል

በዚሁ ከመቀጠላችን በፊት ግን አግባብ ያለውን የውሉን ክፍል ባጭሩ መመልከት ጠቃሚነት ስለሚኖረው ወደዚያው እንመለሳለን ።

በ1842 ዓ.ም. እንግሊዝና ኢትዮጵያ የተፈራረሙት ውል በሁለቱ አገሮች መካከል የተደረገ የንግድና የወዳጅነት ውል ነበር ። [14]

ውሉ 19 አንቀጾች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያዎቹ 16 አንቀጾችና የመጨረሻው የውሉ አንቀጽ በሸዋና በእንግሊዝ መካከል ኅዳር 7 ቀን 1834 ዓ.ም.[15] በሸዋ ዋና ከተማ በአንጐለላ በሸዋው ንጉሥ በሳህለ ሥላሴና በካፒቴን ሐሪስ መካከል ከተፈረመው ባለ 16 አንቀጽ ውል ጋር አንድ የተመሳሰሉ ነበሩ ።

አንቀጾቹ በአብዛኛው የሚናገሩት በሁለቱ አገሮች መሐል ስለዲፕሎማሲያዊ ወኪሎች ልውውጥና የንግድ ግንኙነቶች ስለሚካሄዱበት ሁኔታዎች እንደዚሁም አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ምን ያህል ቀረጥ መጣል እንዳለበትና የአከፋፈሉን ሁኔታና ሥርዓ አወሳሰን ጉዳይ ነው ።

ነገር ግን በነዚህ አንቀጾች እንደተደነገገው የግንኙነቱ መሰረት ሁለቱን አገሮች እኩል ከመጥቀም ይልቅ ወደ እንግሊዝ ያዘነበለና የእንግሊዝን ጥቅምና የበላይነት በኢትዮጵያ ውስጥ ለማራመድ የሚያስችል ሁኔታ ሽፋንፋን ባለ መልኩ የተቀነባበረበት ነበር ።

ነገር ግን ይበልጥ ተዋራጅ የሚደርገው የውሉ ክፍል ጠንቀኛ በሆነው 17 [16] ቁጥር ሥር የተመለከተው የውሉ ቃል ነው ።

ውሉ የተጻፈው በእንግሊዝኛና በአማርኛ ቋንቋዎች ሲሆን ይህም በያንዳንዱ ገጽ ላይ ጐን በጐን ሰፍሮ ነበር ። ሆኖም በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል ግጭት ሲነሳ የየትኛው ቋንቋ የውል ቃል የበላይነት ማግኘት እንዳለበት ውሉ ፍንጭ የሌለውና አንቀጽም ያልያዘ ነበር ። ግጭት ግን በእርግጥም ነበር ። ግጭቱም የተከሰተው በዚሁ በአንቀጽ 17 ውስጥ ሆኖ የእንግሊዝን ቆንሲል የመዳኘት ሥልጣን በሚያዳክም ሁኔታ ነበር ።

የአንቀጹ የመጀመሪያና የመጨረሻ ክፍሎች ሁለቱም ቋንቋዎች በተዋጣ መልክ የተስማሙበት ነበሩ ። ሆኖም ልክ አውቆ የተሠራ ይመስል ስለ ቆንሲሉ ሁለተኛ የዳኝነት ሥልጣን የሚናገረው በአማርኛው ጽሑፍ አንቀጽ 17 አጋማሽ ላይ የሚገኘው ክፍል የእንግሊዝኛው ጽሑፍ ፍጹም ተቃራኒ ነበር ። በአማርኛው ጽሑፍ ውስጥ ይህ ክፍል እንዲህ ይላል ።

> . . . . . በማንም ነገር ጠብ ቢነሳ ሙግትም በእንግሊዝ ዜጐች ቢነሳ ወይ በእንግሊዝ ዜጐችና በሐበሻ ንጉሥ ዜጐች ማኸል ወይ በእንግሊዝ ዜጐችና በሌላ አገር ዜጐች መሐል ቢነሳ በንጉሥ ሀበሻ ግዛት የሀበሻ ንጉሥ* ቆንሲል ወይ ሌላ በዚያ የተሾመው ይሰማና ይዳኝ . . .

እንደ አማርኛው ጽሑፍ አንቀጽ 17 ከሆነ የሁለት ቆንስሎች መኖር የታሰበ ይመስላል ።

የመጀመሪያው የእንግሊዝ ቆንሲል ሲሆን በሀበሻ ምድር በብሪታንያ ዜጋ የተፈጸመን ማንኛውም ወንጀል እሚዳኝ ነው ፡ ሁለተኛው ደግሞ የሀበሻ ንጉሠ ነገሥት ቆንሲል ሲሆን በብሪታንያ ዜጐች መሐል ወይም በሀበሻ ዜጐችና በብሪታንያ ዜጐች መካከል ወይም በብሪታንያ ዜጐችና በማንኛውም ሌላ አገር ዜጐች መካከል የሚኖርን ክርክር ወይም ሙግት የሚሰማና የሚወስን ነው ።

---

* መስመር የተጨመረ

ሕጉ እንዳለ በሥራ ላይ ይዋል ቢባል የዳኝነት ሥልጣን ድልድሉ በወንጀልና በፍትሐ ብሔር ነገሮች መካከል ክፍፍል ለማድረግ ታቅዶ የተደረገ ይመስላል ። በዚህም ሁኔታ የብሪታንያ ቆንሲል የመዳኘት ሥልጣን የብሪታንያ ዜጐች ያሉበትን የወንጀል ጉዳዮችን ከመስማትና ከመወሰን ባሻገር ፈቀቅ የሚል አይሆንም ። በፍትሐ ብሔር ነገሮች ላይ ያለውን ሥልጣን በአማርኛው አንቀጽ የተገፈፈው ቆንሲል በእንግሊዝኛው አንቀጽ እንዲኖረው ከታሰበው ሥልጣኑ ጋር ተነጻጽሮ ሲታይ የኰሰሰና የደከመ ሆኖ ይገኛል ።

በዚህ መለያየት ተጠያቂ የሆነው ጀብደኛ ወይም መሠሪ ማን መሆኑ በይፋ አልታወቀም ። እንዲሁም የአተረጓጐም ስህተት ይሁን ፣ የአጻጻፍ ስህተት ወይም ራስ ዓሊን ለማግባባት ሆን ተብሎ የተደረገ አሳቻ ዘዴ ስለመሆን አለመሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ነገር የለም ። ውሉ ስለተፈረመበት ሁኔታ የሚተርከው የፕላውዴ ንም ጽሑፍ ቢሆን ይህን ችግር በተመለከተ እምብዛም የሚረዳ አይደለም ። ከዚህም በላይ ሁለቱ መንግሥታት ውሉን በተመለከተ ከዚያ ወዲህ በተለዋወጧቸው መልዕክቶቻቸው ላይ የአንቀጾቹን አለመጣጣም አስመልክተው ያነሱት ነገር የለም ።

ሆኖም ግን ልዩነቱ የትርጉም ስህተት ውጤት እንደነበረ ወይም በምንም ዓይነት ፕላውዴን ተቀብሎት የገባ እንዳልነበረ የሚከተሉት ነጥቦች ሊጠቁሙ ይችሉ ይሆናል ።

1. — በመጀመሪያ ደረጃ ውሉ የተዘጋጀው በእንግሊዝኛ ሲሆን የፕላውዴን ሥልጣንም መሠረታዊ ለውጥ ሳያደርግበት በሀበሻ መሪዎች ውሉን ማስፈረም ነበር ። የአማርኛው አንቀጽ የውል ቃል የተጻፈው ሆን ተብሎ ከሆነ በእርግጥም እላይ ከተገለጸው ሥልጣን ውጭ የተደረገ ነው ።

2. — የእንግሊዝ ዜጐች ተከራካሪ የሆኑበትን የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን ለመስማትና ለመወሰን ሥልጣን ያለው የሀበሻ ሰው የሀበሻ ንጉሥ ቢሾም የሚቻልና ተቀባይነትም ያለው ነገር ነው ።
ነገር ግን ይህን የመሰለን ሹም ቆንሲል ብሎ መሰየምና " ማንም ቢሆን ከሀበሻ ሹማምንቶች ሳይነጋገሩበት ሳይግባቡበት ሳያስቸግሩት ሙግት ሲጀምር ወይ ሲሟገት ወይ ሲጨርስ " የሚል ገደብ የለሽ ነጻነት በአንድ ዓለም አቀፍ ውል ውስጥ መስጠት እንግዳና ያልተለመደ ጉዳይ ነው ። ውሉ ንጉሡ የውጭ አገር ሰው ለዚህ ቦታ እንዲመደብ ወይም የእንግሊዝን ቆንሲል ለዚህ ሥራ በተጨማሪ እንዲሾመው ስለማያስገድድ የተለየ ሁኔታ ለመገመትም አስቸጋሪ ነው ።

3. — ራስ አሊ ውሉን እንዲፈርሙ በጣም ከፍተኛ ጥረት ያደረገው ፕላውዴን ውሉን ወደ አማርኛ ያስተረጐመው በራሱ ጸሐፊ ነው ። ውሉን ለራስ አሊ ያስነበበውም በዚሁ በጸሐፊው አማካይነት ነበር ።

በዚህም የተነሳ ውሉን በእንግሊዝኛው በተጻፈበት ሁኔታ ለማቅረብም ሆነ ራስ ዓሊ እንዳለ እንዲቀበሉት ለማግባባት ወይም ለመለመን አጋጣሚው ለፕላውዴን አመቺና ተስማሚ ነበር ።

ሁኔታው እንዲህ የተመቻቸለት ሆኖ እያለ ፕላውዴን በራሱ ነጻ ውሣኔ ከመጀመሪያው የውሉን የአማርኛ አንቀጽ 17 ትርጉም ጸሐፊው እንዲያለዝበውና እንዲያደክመው ሥልጣን በመስጠት ወይም በማዘዝ መደራደሪያውን ያዳከማል ብሎ ማሰብ በጣም ያስቸግራል ።

4. — እንዲሁም የውሉ የአማርኛው አንቀጽ 17 አቀራረጽ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መሐል የተደረሰ መግባባት ውጤት ነው ለማለት ምንም ፍንጭ ወይም መረጃ የለም ። ከአማካሪዎቻቸው ስለ ውሉ ምክር መጠየቃቸው የሚያጠራጥረው ራስ ዓሊ ውሉን ከመጤፍ ስላልቆጠሩት ለመዋዋል የነበራቸው ፍላጐት እጅግ የቀዘቀዘ ነበር ።

በዚህም የተነሳ በውይይቱ ወቅት ትርኪ ምርኪ ነገሮችን እያነሱ ስላስቸገሩ በጸሐፊው የሚነበበውን የውል ቃል ልብ ብለው እንዲያዳምጡ በፕላውዴን መለመን ነበረባቸው ።

ለራስ አሊ ውሉ ከተነበበላቸው በኋላ ፦—

. . . . . . የኔ ማብራሪያና መግለጫ ታክሎበት ሰነዱን ዘለቅነው ከዛም ሰነዱ በያዘው ነገር ምንም ጉዳት እንዳላዩበት ራስ ተናገሩ ። ቀጥሎም ሁለቱን ቅጂዎች በማህተማቸው ካተሙ በኋላ የራሳቸውን ድርሻ ለሚያቀርቡት እንደ ደብተራ ሰጥተው ደብረ ታቦር ወስዶ እንዲቆልፍበት አዘዙ ።

ሲል ፕላውዴን ገልጧል ።

ፕላውዴን ለራስ ዓሊ የገለጠው ስለምን መሆኑን ወይም ገለጣው አንቀጽ 17ን መጨመር አለመጨመሩን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው ። የራስ ዓሊን ግድየለሽ አእምሮ እያስጨንቅ እንጂ ራስ ዓሊ ማህተማቸውን ከውሉ ግርጌ ሲያኖሩ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል በተለይ አንቀጽ 17ን በተመለከተ የአእምሮ መገናኘት የነበረ መሆኑን ለማወቅም እንደዚሁ አስቸጋሪ ነው ።

ፕላውዴንን በተመለከተ ግን ማህተም ያረፈበትን የራሱን ድርሻ በጁ ጨብጦ ከራስ ዓሊ የውስጥ ድንኳን ሲወጣ ውሉን በመመሪያው መሰረት በማስፈረሙ ኃላፊነቱን በተሳካ መልክ ከመወጣት ስሜት ጋር መሆኑን መገመት ይቻላል ። የአንቀጽ 17 የውሉ የእንግሊዝኛው ጽሑፍ እንደሚከተለው ተቀምጧል ፦—

የሐበሻ ንጉሠ ውል ይሠር ፡ በምንም ነገር በግዛቱ ሐበሻ የእንግሊዝ ዜጐች በማንም ነውር በተከሰሱ ጊዜ በእንግሊዝ ንግሥት ኩንስል ይዳኝ ወይ በሌላ ሹም የእንግሊዝ ንጉሠ በዚያ የሾመው ፥ በማንም ነገር ጠብ ቢነሳ ሙግትም በእንግሊዝ ዜጐች ቢነሳ ወይ በእንግሊዝ ዜጐችና በሐበሻ ንጉሥ ዜጐች ማኸል ወይ በእንግሊዝ ዜጐችና በሌላ አገር ዜጐች መሐል ቢነሳ ፡ በንጉሠ ሐበሻ ግዛት የእንግሊዝ ንግሥት * ኩንስል ወይ ሌላ በዚያ የሾመው ይሰማና ይዳኝ ማንም ማን ቢሆን ከሐበሻ ሹማምንቶች ሳይነጋገሩበት ሳይገቡበት ሳያስቸግሩት ሙግት ሲጀመር ወይ ሲሟገት ወይ ሲጨርስ

በዚህ አንቀጽ መሰረት የብሪታንያ ቆንሲል ወይም ለዚሁ ጉዳይ በብሪታንያ መንግሥት የተሾመ ሌላ የብሪታንያ ባለሥልጣን የሚከተሉትን ለመፈጸም ሥልጣን አለው ።

---

* አማርኛው — የሐበሻ ንጉሥ ይላል ።

1. — በሐበሻ ንጉሥ ግዛት በማናቸውም ክልል ውስጥ አንድ የብሪታንያ ዜጋ ነውር ሰርቶ በተከሰሰ ጊዜ ጉዳዩን መስማትና መወሰን ፤

2.. — በሐበሻ ንጉሥ ግዛት ውስጥ ማናቸውም ጠብ ወይም ሙግት ፤
 ሀ/ በእንግሊዝ ዜጐች መካከል ቢነሳ ፤
 ለ/ በእንግሊዝ ዜጐችና በሐበሻ ንጉሥ ዜጐች መካከል ቢነሳ ፤
 ሐ/ በእንግሊዝ ዜጐችና በማንኛውም ሌላ የውጭ መንግሥት ዜጐች መሐል ቢነሳ መስማትና መወሰን ፤

በዚህ አንቀጽ ውስጥ አንድ ግድፈት አለ ። ይኸውም የብሪታንያ ዜጋ የወንጀል ፈጻሚ በመሆን ፋንታ የወንጀል ሰለባ ሲሆን አቤቱታውን የት እንደሚያቀርብ አንቀጹ ለይቶ አለመናገሩ ነው ። ሁኔታው ከውሉ ዓላማ አኳያ ሲታይ ግድፈቱ የመጣው ካለማስተዋል እንጂ በሐገሪቱ ለነበረው የዳኝነት ሥርዓት ከበሬታ ተብሎ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል ።

ለማንኛውም ቆንሲሉ የእንግሊዝ ዜጐች ተከራካሪ ሆነው በሚቀርቡበት " ጠብ ወይም ሙግት " ሁሉ የተሟላ የዳኝነት ሥልጣን በውሉ የተጐናጸፈ ስለሆነ የአንቀጹ የመጀመሪያው ክፍል ጠባብ አቀራረብ የቆንሲሉን የዳኝነት ሥልጣን ይገድበዋል ለማለት ፈጽሞ የማይቻል ነው ።

በአንቀጽ 17 ለተዘረዘሩ ጉዳዮች የመዳኘት ሥልጣን የተጐናጸፈው የእንግሊዝ ቆንሲል ወይም ሌላ ሹም ከዚሁ ጋር አያይዞ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባውን ሕግ የመወሰን ተጨማሪ ሥልጣን ያለው ይመስላል ። ይህን በተመለከተ ሕጉ ምንም እስካላለ ድረስ የቀረቡለትን ጉዳዮች ሁሉ በራሱ አገር ብሔራዊ ሕግ መሰረት የመወሰን ሥልጣን በዝምታ ሰጥቶታል ማለት ይቻላል ። ይህም በአጭሩ የነበረውን የሀገሬውን ባህል ወይም የሕግ ሥርዐት እንደሌለ መቁጠር ማለት ነው ። የዚህ ዓይነት አሠራር ለብሪታንያ ዜጐች በተለይም የወንጀል ድርጊትን በተመለከተ ለክስ እንዳይጋለጡ በማድረግ ያለው የመከላከል ውጤት ግልጽ ነው ። የአንድ ድርጊት መፈጸም ወይም አለመፈጸም ወንጀል የሚሆነው የሀበሻ ሕግ ወይም ባህል እንዲያ ስለሚያደርገው ሳይሆን የዚያ ዓይነት ተግባር በብሪታንያ የሕግ ሥርዓት ወንጀል ነው ተብሎ በመደንገጉ ብቻ ይሆናል ። የዚህም ግልጽ ውጤት ለቆንሲሉ የዳኝነት ሥልጣን መስጠት ብቻ ሳይሆን የእንግሊዝን ምግባረ ግዕዛት የተለየ ሁኔታ ባለበት አገር ውስጥ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ማድረግንም ይጨምራል ።

ባጭሩ አንድ የብሪታንያ ዜጋ በሀበሻ አገር እየኖረ እንግሊዛዊ በመሆኑ ብቻ በእንግሊዝ ምግባረ ግዕዛት (ሕግ) እንዲተዳደር ተፈቅዶለታል ማለት ነው ። ይህ በመሆኑም ከእንግሊዝ ሕግ ጋር የማይስማማውን ማናቸውንም የሀበሻ ምግባረ ግዕዛት የማክበርም ሆነ የመጠበቅ ግዴታ አይኖርበትም ማለት ነው ። ይህ ሁኔታ አንድን የብሪታንያ ዜጋ የሚያጋጥመውን የፍትሐ ብሔርም ሆነ የወንጀል ሙግት በሀበሻ ሕግ መሰረት እልባት እንዲያገኝ ወይም የሽምግልና ግልግልን በመሳሰሉ የዳበሩ ባህላዊ ዘዴዎች ተጠቅሞ ለመጨረስ የሚገፋፋው አይሆንም ።

ስለ እንግሊዝ ቆንሲል ወይም ሹም የመዳኘት ሥልጣን የሚናገሩት ቀሪዎቹ ሶስት ሁኔታዎች የሚመለከቱት የፍትሐ ብሔር ነገሮችን እንደሆነ በአንቀጹ በኋለኛው ክፍል " ጠብ ወይ ሙግት " በማለት ከተጠቀሱት ቃላት መገመት ይቻላል ። ከነዚህም ውስጥ የመጨረሻዎቹ ሁለቱ የብሪታንያ ዜጐች ያልሆኑ ሰዎችን

መብት ሊነኩ በሚችሉ ክርክሮች ላይ የመፍረድ መብት ለብሪታንያ ቆንሲል ይሰጣሉ ። በነዚህ ጉዳዮች ላይ የእንግሊዝ ቆንሲል የመዳኘት ሥልጣን የሚኖረው ከባለጉዳዮቹ አንዱ የብሪታንያ ዜጋ በመሆኑ ብቻ ነው ። በመሆኑም የሌሎች ባለ ጉዳዮች ዜግነት እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የቀረቡት በከሣሽነት ይሁን ወይም በተከሣሽነት ግምት ውስጥ የሚገባ አይሆንም ።

እንግዲህ ይህ ሁኔታ የእንግሊዝ ዜጋ ያልሆነውን ተሚጋች በአገሩ ሕግ መሠረት ለችግሩ እልባት በመፈለግ ፋንታ ክሱን ለመመሥረት ቆንሲሉ እሚኖርበት ድረስ መሄድ እንዳለበትም ይጠቁማል ። ይህም ብዙ የሀበሻ ባለጉዳዮችን ጉዞው ከሚያስከትለው ወጭ ለመዳን ወይም በባዕድ ዳኛ ፊት ቆሞ መከራከር ከሚፈጥረው ችግር ለማምለጥ በእንግሊዝ ዜጎች ላይ ክስ እንዳይመሰርቱ የመገፋፋት ዝንባሌ ሊኖረው እንደሚችል ይታመናል ።

ቆንሲሉ “ ጠብ ወይም ሙግት ” ቀርቦለት በሚያከራክርበት ወቅት የራሱን አገር ሕግ ተፈጻሚ እንዳያደርግ ውሉ አሁንም ቢሆን ሥልጣኑን የሚገድብ አንቀጽ አልያዘም ። የሀበሻም ሆኑ የእንግሊዝ ዜጎች ባልሆኑ ሰዎች ላይ ለእንግሊዝ ቆንሲል የመዳኘት ሥልጣን የሚሰጠው የውሉ አንቀጽ የሌላ 3ኛ መንግሥትን ጥቅም የሚነካ በመሆኑ ሁለቱም መንግሥታት ሊደራደሩ የማይችሉበት ነጥብ ነበር ።

ተፈጻሚነት ስለሚኖረው ሕግ የማይናገረው ውል ቆንሲሉ በሚሰጠው ፍርድ ላይ የይግባኝ መብት ስለመኖሩም የሚወስነው ነገር የለም ። ይግባኝ ቢፈቀድ እንኳ ይግባኝ ሰሚው ማን እንደሚሆንም አይገልጽም ። ቆንሲሉ በሥልጣኑ ሥር ያሉ ጉዳዮችን በሙሉ ሰምቶ እንዲወስን ፡—

> ማንም ማን ቢሆን ከሐበሻ ሹማምንቶች ሳይናገሩበት ሳይገቡበት ፡ ሳያስቸግሩት ሙግት ሲጀምር ወይ ሲያሟግት ወይ ሲጨርስ

በማለት ውሉ ስለሚደነግግ ፤ የቆንሲሉን ውሳኔ በይግባኝ የሚሰማ አካል ለመፍጠርም ሆነ ጨርሰውንም የይግባኝ መብት እንዲኖር የማድረግ ፍላጐት አልነበረም ለማለት የሚያስችሉ ምክንያቶች አሉ ። በተጨማሪም የአንቀጹ አቀራረብ የቆንሲሉን ሥልጣን ከመዳኘት ክልል አሳልፎ ወደ ፍርድ አፈጻጸም መድረክም ስለሚያሸጋግረው የሥልጣኑ ስፋት አንድና ሁለት የማይባል ነው ።

ቆንስሉ በውሉ አንቀጽ 18 የሚከተለው ተጨማሪ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

> የእንግሊዝ ዜጋ በሐበሻ ግዛት የሞተ እንደሆነ . . .
> የሞተውን ሰው ወረቀቱን ገንዘቡን ይቀበላል ፡ ብድር ቢኖርባቸው ወራሽ ቢኖራቸው ባለዳ ቢኖርባቸው ወስዶ እንዲሰጣቸው የሐበሻ ሹማምንት ሳያስቸግሯቸው ።

እዚህም ላይ በድጋሚ የሟቹ እንግሊዝ ወራሾች ወይም አበዳሪዎች ዜግነት እግምት ውስጥ አልገባም ። የእንግሊዝ ቆንሲል የሕጐች መጋጨትን ሊያስከትሉ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ምናልባትም የራሱን አገር ሕግ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችል ሥልጣን በድጋሚ ተሰጥቶታል ።

በመጨረሻም የዚህ የተዛባ የውል ሁኔታ ጥብቅ አፈጻጸም “ የዘለዓለም ወዳጅነት በሁለቱ ነገሥታቶች ማኸል ያቆማል ” ተብሎ በአንቀጽ 19 ላይ ተመልክቷል ። ውሉ ለምን ያህል ጊዜ ጸንቶ እንደሚቆይ ፤ ወይም በምን ሁኔታ ማፍረስ

እንደሚቻል በውሉ ላይ የተመለከተ ነገር የለም ። በዚህም የተነሳ ውሉን ቀሪ ለማድረግ ያለው መንገድ የሁለቱን መንግሥታት ስምምነት የሚጠይቅ ይሆናል ። ለዚህም በታላቋ ብሪታንያ በጐ ፈቃድ ላይ መተማመን ግዴታ ይሆናል ። በወቅቱ በነበረው ሁኔታ ደግሞ ያንን ከታላቋ ብሪታንያ መጠበቅ የማይመስል ነገር ነበር ።

## ቴዎድሮስና የ1842 ዓ.ም. ውል

ፕላውዴን ይህን የመሰለ የውል ሁኔታ ራስ ዓሊን እንዲቀበሉ ያግባባቸው ያለ ብዙ ችግር ነው ።[17] በ1847 ዓ.ም. አጼ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ሲገኙ በ1842 ዓ.ም. የተፈረመውን ውል እንደገና ለመደራደርም ሆነ በሥልጣን የተቀመጡት ንጉሥ እንዲቀበሉት የመጠየቅ ሀሳብ አልነበረውም ። የውሉ ጉዳይ ያለቀ የደቀቀ ስለነበር ቴዎድሮስ ውሉን የመቀበልና የማክበር ግዴታ አለባቸው በማለት ፕላውዴን ያምን ነበር ።

ይህንንም ፕላው ዴን ለው ጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ሰኔ 18 : 1847 ዓ.ም. ከጻፈው ደብዳቤ መረዳት ይቻላል ። አግባብ ያለው የዚየ ደብዳቤ ክፍል እንደሚከተለው ይነበባል ።[18]

> በመሄጃዬ ቀን ዋዜማ ምሽት የመጣሁበትን ዓላማ ለማወቅ ንጉሡ መልእክት ላኩብኝ ፤ እኔም በመንግሥቴ ተልኬ ወይም መንግሥትን ወክዬ አለመምጣቴን ገልጬ ወደ ሀገሬ ስለምሄድ የቆንሲል መሥሪያ ቤት ስለማቋቋምና ባጠቃላይም በሀገሮቻችን መካከል የወዳጅነት ግንኙነት ለመፍጠር ንጉሥ ያላቸውን ሀሳብ ማወቅና ለመንግሥቴም ማሳወቅ እንዳለብኝ አስረድቼ ፥ ከራሴ ዓሊ ጋር ስለተደረገውም ስምምነት ጠቆም አደረግሁ ።

ፕላውዴን በልበ ሙሉነት ለተናገረው ቃል ንጉሡ የሰጡት ምላሽ ሳያስደነግጠው እንዳልቀረ መገመት ይቻላል ።

> "ራስ አሊ ምን እንደሁኑ" አሉ ቴዎድሮስ "የማውቀው ነገር የለም . . . በቀደሙት የሀበሻ ነገሥታት ጊዜም የቆንሲል መሥሪያ ቤቶች ስለመኖራቸው የሰማሁት ነገር የለም ፤ ስለዚህ ይህ ጉዳይ እንዲመከርበት ለአማካሪዎቼና ለሹማምንቶች መቅረብ ያለበት ነው ።"[19]

እንግዲህ ቴዎድሮስ ስለውሉ ያላቸውን አቋም ባጭሩና በጠራ መልክ የገለጡት በዚህ ሁኔታ ነበር ። መልሳቸውም አዎንታዊና አሉታዊ ነጥቦችን አጣምሮ የያዘ ነው ። በማያውቁትና ተዋዋይ ሆነው ባልፈረሙት ውል አልገደድም ማለታቸው አሉታዊ መከራከሪያቸውን የሚያንጸባርቅ ነው ። በወቅቱ በነበሩት ሁኔታዎች አንጻር በርግጥም አጼ ቴዎድሮስ ውሉን ሳያውቁ መቻላቸው ሊሆን የሚችል ነገር ነው ።[20]

የውሉን መኖር አውቀው ቢሆን እንኳ ኖሮ "ራስ ዓሊ በፈጸሙት ድርጊት" መገደድ ስለማይገባቸው ውሉን ለማክበር ዝግጁ አልነበሩም ።

ዓሊን በጦር ኃይል አስወግደው ሥልጣነ መንግሥቱን የተረከቡት ቴዎድሮስ ከሥልጣን የተባረሩት የራስ አሊ ወራሴ መንግሥት ወይም ሕጋዊ ተተኪ እንደ

ሆኑ ተቆጥረው ራስ ዓሊ የገቡትን የውል ግዴታ በሕግም ቢሆን የማክበር ኃላ ፊነት ጨርሶ ስለሌለባቸው ውሉን አልቀበልም ማለታቸው የተገባና ትክክል ነበር ። ይህ ውል በውርስ ሊተላለፍ አይችልም የሚለው አቋም ቀረ ቢሆን እንኳ “ በቀደሙት የሀበሻ ነገሥታት ጊዜም የቆንሲል መሥሪያ ቤቶች ስለመኖራ ቸው” ቴዎድሮስ የሚያውቁት ነገር ስለሌለ ውሉን ለመቀበል ፈቃደኛም ዝግጁም አልሆኑም ። ባጭሩ የቆንሲል መሥሪያ ቤት የማቋቋሙን ጥያቄ ቴዎድሮስ ያል ተቀበሉት በሀበሻ ታሪክ ውስጥ ያልተመዘገበ “ አዲስ ” ክስተት ሆኖ ስላገኙት ነው ።

ራስ ዓሊ ባደረጉት ውል አልገደድም በማለትና ከዚያም በፊት በሀበሻ ታሪክ ውስጥ ያልተመዘገበ እንግዳ መሥሪያ ቤት እንዲቋቋም አልፈቅድም ሲሉ ቴዎድሮስ የሰጡት መልስ ፕላውዴንን ዙሪያውን ገደል ስላደረገበት ሀሳቡን ለማ ጠናከር መፈናፈኛ ሊያገኝ አልቻለም ። ቴዎድሮስ ካነሷቸው ነጥቦች መካከል አንዳንዶቹ ተከታታይ ሁኔታዎችን ጭምር አስቀድመው የሚነኩ ስለነበሩ እን ግሊዞች ከዚያ ወዲህ እንኳ የሰነዘሯቸውን ነቀፌታዎች የሚያከሽፉ ነበሩ ። ለም ሳሌ መስከረም 25 ቀን 1858 ዓ.ም. አርል ረስል ለኰሎኔል ሰታቶን በጻፈው ደብ ዳቤ ላይ የሚከተለው ይገኛል[21] ።

> ንጉሡ በ1842 የተፈረመውን ውል አላከብርም ማለት ብቻ ሳይ ሆን የውሉን መኖር ለመቀበል አሻፈረኝ ብለዋል ። ንጉሡ የው ሉን መኖሩ የመቀበል የቅን ልቡና ግዴታ እንዳለባቸውና የማይ ስማሙበት አንቀጽ ቢኖር ግን የማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብ እንደ ሚችሉ ለቆንሲል ፕላውዴን በ1850 የእንግሊዝ መንግሥት ገል ጦለት ነበር ።

ፕላውዴን ከዚህ ሁለት ዓመት ቀደም ብሎ የንጉሡን መልስ ጠቅሶ ባስተላ ለፈው ሪፖርት ላይ የገለጠው ሲታይ ከላይ የተሰነዘረውን አስተያየት የሚደግፍ ፍንጭ አይገኝም ። ስለ ውሉ የቴዎድሮስ ተቃውሞ ግልጽና የታወቀ ነበር ። እንዲህ በማለትም እንደመስተዋት አጥርተው አስቀምጠውታል ።

> በታሪካችን ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ነገር ስለሌለ የቆንሲል መሥሪያ ቤት እንዲቋቋም አልፈቅድም ።

የዚህ ግልጥ አቋም መልእክት በጥራት የገባው ፕላውዴን “ ቴዎድሮስ ለቆንሲሉ የመዳኘት መብት የሚሰጠው አንቀጽ ሥልጣኔን የሚገፍ ነው የሚል ሥጋት አሳድሮባቸዋል ” በማለት ሰኔ 18 ፤ 1847 ዓ.ም. ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ባስተላለፈው ሪፖርት ላይ ገልጦታል ።

አጼ ቴዎድሮስ ውሉን እንዲቀበሉት ለማግባባት ከ1847 ዓ.ም. ጀምሮ ያል ተሞከረ ድርጊት የለም ። ጆን ቤልና በወቅቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ የነበሩት አቡነ ሰላማም[22] በአማላጅነት ተልከዋል ። በንጉሡና በፕላውዴን መካከልም በተካሄደው ቀጥታ ውይይት አማካይነት ንጉሡን ለማግ ባባት ተሞክሯል ። ሌላው ቀርቶ ቴዎድሮስ ውሉን ቢቀበሉ ተጨማሪ ግዛት እን ደሚሰጣቸው ተገልጦላቸዋል ።

ስለዚህም ፕላውዴን እንዲህ ይላል ።

> ውሉን ለመቀበል ከፈቀዱ የባህሩ ጠረፍና ምጽዋ ሊሰጣቸው እንደሚችል ለመጠቆም ደፍሬአለሁ ።

ይህ ሁሉ የተደረገው በእንግሊዝ ተረቅቆ የቀረበውን የ1842 ዓ.ም. ውል ያለምንም ለውጥ አጼ ቴዎድሮስ እንዲቀበሉት ለማግባባት ነው ።

ይሁን እንጂ የቴዎድሮስ አቋም በጽኑ ዓላማ ላይ የተመሠረተ ነበር ። ከታላቋ ብሪታንያ ጋር ለመወዳጀት ፈቃደኛም ዝግጁም ነበሩ ። በዚህም የተነሳ ወደ አውሮፓ ኃያላን መንግሥታት አምባሳደሮቻቸውን ለመላክ ሀሳብ አቅርበው ነበር ። ሆኖም ከዚሁ ጋር ያቀረቡት አንድ ዋና ሁኔታ " ከነዚህ መንግሥታት ጋር መወዳጀት የሚገባን በእኩልነት ደረጃ ነው "[23] የሚል ነበር ።

ሥልጣን እንደጨበጡ ከወሰድዋቸው እርምጃዎች አኳያ ነገሩ ሲታይ ያነሱት የዕኩልነት ጥያቄ ከዋልተር ፕላውዴን ሳይቀር ድጋፍ አስገኝቶላቸዋል። ። ዋልተር ፕላውዴን ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ሲጽፍ እንዲህ ብሏል[24]።

> ነፍሰ ገዳዮችን ለሚች ወገኖች አሳልፎ የመስጠትን የጭካኔ አሠራር አስወግደው የሞትም ሆነ የመሰየፍ ቅጣት በአደባባይ እንዲፈጸምባቸው አጥፊዎች ለመንግሥት ሹሞች እንዲሰጡ አድርገዋል ።
>
> በየአውራጃው የሚገኙ ወታደሮች ሁሉ የመዳኘትና የመቅጣት ሥልጣንን ሳይጨምር ከፍተኛ ማዕረግ በሰጧቸው ታማኝ ተከታዮቻቸው ሥር እንዲሆን አድርገዋል ።
>
> በዚህም በንጉሣቸው ሳይሆን በዘራቸው የሚኩራሩትን የፊውዳል ባላባቶች አስወግደው ጀኔራሎችን ተክተዋል ። ንግድን በተመለከተ በየቦታው ይደረግ የነበረውን አሰልቺ ክፍያ አስወግደው በግዛታቸው ውስጥ በሶስት ሥፍራ ብቻ ግብር እንዲከፈል ወስነዋል ። እነዚህ ጥረቶች ሁሉ ባንድ ጊዜ ያለህጸጽ ተፈጻሚ ይሆናሉ ማለት ያስቸግራል . . . ሰይፍንና ጦርን ወደ ማረሻና ማጭድ እለውጣለሁ ፤ አራሽ በሬም ከተመሰገነ ሰንጋ ፈረስ የበለጠ ዋጋ እንዲያወጣ አደርጋለሁ ብለዋል ።

በሌላ በማንም ሳይሆን በራሱ በእንግሊዝ ቆንሲል የተሰጠው ይህ ምስክርነት እንግሊዝ በሀበሻ ምድር ዜጎቿን ለመዳኘት እንድትችል ያቀረበችውን ጥያቄ የሚያዳክም ነው ።

ምስክርነቱ በሀበሻ ለሚኖሩ ባዕዳን የተለየ ጥበቃ የማያስፈልጋቸው መሆኑን ስለሚጠቁም እንደዚያ ያለውን ስምምነት ጠቀሜታ ቢስ ያደርገዋል ። ይህም ባዕዳን በሙሉ እንግሊዞችንም ጨምሮ ሀበሻ ምድር ከገቡ በኋላ በወቅቱ በሀገሪቱ በነበረው ምግባረ ግዕዛት እንዲተዳደሩና እንዲዳኙ ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው ። እንደሚገመተው ቴዎድሮስ ለራሳቸው ጀኔራሎች እንኳ የነፈጉትን የዳኝነት ሥልጣን ለባዕድ ቆንሲል አሳልፈው ለመስጠት ፈጽሞ ዝግጁ አልነበሩም ።

የቆንሲሉን የዳኝነት ሥልጣን አለመቀበላቸው ከውጭ መንግሥታት ጋር መገናኘት ያለብን በእኩልነት ደረጃ ነው ብለው ከያዙት አቋም ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው ። ከእኩልነት ያነሰ ምንም ነገር እንደማይቀበሉ ደጋግመው አስገንዝበዋል ። ይህን በተመለከተ ፕላውዴን ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበር ።

> ሉዐላዊ መብታቸውን የሚቀናቀን መስሎ በሚታያቸው በማና ቸውም ነገር ላይ እንደሚገመቱው ሁሉ ቀናኢነታቸው እጅግ ከፍተኛ ነው ።

ይህም የፕላውዴን አስተያየት ቴዎድሮስ ባንድ አጋጣሚ ሥልጣንን በተመለከተ በመዘበት መልክ ከእግዜር ጋር አድርገናል ስላሉት ውል በተናገሩት ቃል የተደገፈ ነው ። [25]

> እግዚአብሔር መሬት ወርዶ እንዳይቀጣኝ እኔም ሰማይ ወጥቼ እንዳልወጋው ተስማምተን ውል ገብቻለሁ ።

ለእንግሊዝ ቆንሲል የዳኝነት ሥልጣን እንዲሰጥ የቀረበው ጥያቄ ንጉሡ ሉሀላዊ መብታቸውን ለእግዚአብሔር ጭምር እንኳ ሳያጋሩ ለመያዝ ካላቸው ቁርጠኝነት ጋር የማይስማማ መሆኑ ፍጹም ገሃድ ነው ።

እንደዚሁም ይህ ስምምነት የማታ ማታ የሚያስከትለው ዞማና ከዚሁ ጋር በማስታከክ ሊፈጸሙ የሚችሉ ደባዎችና መሰሪ ድርጊቶች ከንጉሡ የተሰወሩ አልነበሩም ። ስለ ኢትዮጵያ ሰፊ ዕውቀት የነበረው መሆኑ የሚነገርለት ቻርላስ ቤክ በ1858 ዓ. ም. መጀመሪያ ላይ የንጉሡን እንቢታ ደግፎ እንደሚከተለው ጽፎአል[26]።

> ግብጽንና ቅድስት ሀገርን ጐብኝተው ከተመለሱ የራሳቸው ሀገር ዜጐችና ከባዕዳን ተጓዦችም ከሰሙት የአውሮፓ መንግሥታት ቆንሲሎች በነዚያ አገሮች ስለነበራቸው ከፍተኛ ሥልጣንና ይህም በአገሮቹ ውስጥ ችግር ስለማስከተሉ በሰፊው የሚያውቁ ስለሆነ በቱርክ ግዛት እንዳለው ዓይነት በመንግሥት ውስጥ መንግሥት እንዳይቋቋም ቁርጠኛ አቋም በመያዛቸው ማንም ሊፈርድባቸው አይገባም ።

የቤክን ዘገባ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በመስከረም 1856 በሀበሻ የፈረንሳይ ቆንሲል የነበረውን ኤም ሌጀርንን ሲያስወጡ ከተናገሩትና በራሱ በቆንሲሉ እን ደበት ከተዘገበው መጥቀሱ ይበቃል ። [27]

> የአውሮፓ መንግሥታት የምሥራቅ አገሮችን መያዝ ሲፈልጉ የሚጠቀሙበትን ዘዴ አውቀዋለሁ ፤ መጀመሪያ ሚሲዮናውያንን ይልካሉ ፣ ሚሲዮናውያንን ለመደገፍ ቆንሲሎችን ያስከትላሉ ፤ ቆንሲሎችን ለመጠበቅ ደግሞ ለጥቀው ወታደሮች ይገባሉ ። እኔ በዚህ ዓይነት የምደለል የሂንዱስታን ራጃ (ንጉሥ) አይደለሁም ፤ ውዬ ሳላድር ከጦሩ ጋር መፋለምን እመርጣለሁ ፤

ይህ የሆነው በ1852 ዓ.ም. ከፕላውዴን አሳዛኝ ሞት በኋላ ሶስት ዓመት ቆይቶ ነው ። ፕላውዴን * የሞተው አጼ ቴዎድሮስን የሚያጠግብ የውል ሀሳብ ማመንጨት አቅቶት በምጽዋ በኩል አድርጐ ወደ እንግሊዝ አገር ለመቀጠል በመጓዝ ላይ እንዳለ ነበር ። ፕላውዴን በአምስት ዓመት ቆይታ ቆንሲልነቱን ቴዎድሮስ እንዲቀበሉት ማድረግ ቀርቶ በ1842 ዓ.ም. በተፈረመው ውል ላይ

* ፕላውዴን የተቀበረው በጐንደር ክፍለ ሀገር በግምጃ ቤት ማርያም ቤተክርስቲያን ሲሆን አጽሙም እስከ ዛሬ ድረስ በዚያው አርፎ ይገኛል ።

የተመለከቱትን የንግድና የዳኝነት መብቶች እንኳ ለሀገሩ ማስከበር ተስኖት ስለ ነበረ ጉዞውን የጀመረው ከመከፋት ጋር መሆኑን መጠራጠር አይቻልም ።

## በአበሻና እንግሊዝ አዲስ ውል ድርድር

ፕላውዴንን የተካው ካፒቴን ቻርለስ ዱንካን ካሜሮን ሲሆን " በሀበሻ አገር የግርማዊት ንግሥት ቆንሲል" ሆኖ መሾሙም ሰኔ 17 ፡ 1852 በለንደን ከተማ ይፋ ሆኗል ። አዲሱ ቆንሲል የካቲት 13 ፡ 1854 አርል ረስል ለቴዎድሮስ የጻፉ ውን የመተዋወቂያ ደብዳቤ ይዞ ወደ ምድረ ሀበሻ ጉዞውን ጀምሯል ። አቅራቢው የሚቹ የዋልተር ፕላውዴን ተተኪ መሆኑን ከሚናገር በቀር ስለአከራካሪው ውል ደብዳቤው የያዘው አንደም ነገር አልነበረም [28] ።

አዲሱ ቆንሲል ከርሱ በፊት የነበረው ቆንሲል ካሳረፈበት ሥፍራ ጀምሮ ሥራውን መቀጠል የነበረበት ቢሆንም እንግሊዞች ወደ በስተኋላ ኢትዮጵያን በተመለከተ ያሳዩት የፖሊሲ ማፈግፈግ በጉዳዩ ላይ ውይይቱን ባዲስ መንፈስና በሙሉ ልብ ለመቀስቀስ ካሜሩን ባደረገው ጥረት ውስጥ የተወሳሰቡ ሁኔታዎች ሳያጋጥሙት አልቀረም ። ወዲያውኑ በጥቅምት 1855 ዓ.ም. ጉጃም ላይ እንዳለ አንድ ያላሰበው ዕድል ካሜሮንን አጋጠመው ። ይኸውም ከአጼ ቴዎድሮስ የተላከ ደብዳቤ ሲሆን ፍሬ ሀሳቡም ባስቸኳይ ወደ ምጽዋ ወርዶ ንጉሡ ወደ እንግሊዝ አገር የሚልኳቸውን " መልእክተኞችና አምባሳደሮች ማሳለፍ ይችሉ ወይም አይችሉ " እንደሆነ አጣርቶ እንዲገለጥላቸው ካሜሮንን የሚያሳስብ ነበር ። ካሜሮንም ጊዜ ሳይፈጅ ወዲያውኑ ጥቅምት 19 ፡ 1855 ዓ.ም. ጉጃም ሆኖ በጻፈው ደብዳቤ መልሱን ሰጠ ። ከአሥራ ሶስት ዓመት በፊት ተፈርሞ ግዑዝ ወረቀት ሆኖ የቆየውን ውልም ጉዳይ ለመቀስቀስ ካሜሮን በዚያ አጋጣሚ ሊጠቀም ችሏል ።

ካሜሮን ያቀረበው አዲስ ሀሳብ ከቀድሞው ለየት ያለና ውሉ እንዲጸድቅ የሚጠይቅ ሳይሆን በ1842 ዓ.ም. የተደረገውን ውል ሀ ብሎ ለመደራደር የሚያሳስብ ነበር ።

አግባብ ያለው የዚያ ደብዳቤ ክፍል ሰፋ ባለ ሁኔታ እንደሚከተለው ተጠቅሷል[29] ።

> ለግርማዊነትዎ ስለአምባሲው ያለኝን ሀሳብ ከገለጥሁ በኋላ . . . . ላሳስብዎ የምፈልገው አንድ ነጥብ አለኝ ፤ ይኸውም ግርማዊነትዎ በእኔ እዚህ መገኘት አጋጣሚ በመጠቀም ለኛ ንግሥት የሚቀርብ አንድ የውል ረቂቅ እንዲዘጋጅ የሚስማሙ መሆንዎን ነው ። የግርማዊነትዎ መልካም ፈቃድ ቢሆን በረቂቁ ውል ላይ በጊዜያዊነት ብንፈራረምበት ስለሁኔታው እኔም ለመንግሥቴ አስቀድሜ ለመግለጥ የምችል ሲሆን በጊዜያዊነት የተፈረመው ውል ከአምባሳደርዎ ጋር ሊላክ የሚችል ነው ።
>
> በራስ ዓሊ አማካይነት ከቀድሞው ንጉሥ ጋር የተደረገው የውል ቅጂ በእጄ ስለሚገኝ የግርማዊነትዎ መልካም ፈቃድ ቢሆን ሰነዱ ለአዲሱ ውል መነሻ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ነው ። ሰነዱን አንዳንድ ለውጦች አክየበት ግርማዊነትዎ እንዲያየው ልከዋለሁ ። ፈጥኜ ላሳስብ የምፈልገው ግን ከሚስተር ፕላውዴን ጋር ያልተግባባችሁባቸው ነጥቦች የሚከተሉት መሆናቸውን ነው ።

1. ቆንሲል እንዲኖር መስማማት ፤
2. ቆንሲሉ ተቀባይነት ካገኘ ከቀድሞው ንጉሥ ጋር በተደረገው ውል መሰረት የዳኝነት ሥልጣን ለቆንሲሉ ይሰጥ እንደሆን ፤

ስለመጀመሪያው ግርማዊነትዎን ለመጠየቅ የምፈልገው ባጠቃላይ በወዳጅነትና በእስታራቂነት ያገለገለው በተለይም ለግብጾች ወረራ ለተጋለጡት ያልታደሉ የሀበሻ ነገዶች ጥላ ከለላ የነበረው የፕላውዴን እዚህ መኖር ጠቀሜታ አልነበረውም ወይ በማለት ነው ? በተጨማሪስ ግርማዊነትዎ ብቸኛ የአገሪቱ መሪ እንዲሆኑ ፍላጎቱን በቃልና በተግባር ሳይገልጥ ቀርቷል ? በመጨረሻም የሀበሻን ጥቅም ክብርና ነጻነት የሚጻረር አዝማሚያ ያሳየበት ወቅት ነበር ?

የእንግሊዝ የቴክኒክ ሰዎችን ለማስመጣት ግርማዊነትዎ ፍላጎት እንዳለው ሰምቻለሁ ፤ ሆኖም እነዚህ ሰዎች ደህንነታቸውን የሚጠብቅ ሹም በልዩ መልዕክተኛም ይሁን በቆንሲል ደረጃ ከሌለ እዚሁ መኖር አይችሉም ።

ቆንሲሉ የራሱን ሰንደቅ ዓላማ የሚያውለበልብ ስለመሆኑ ይህ ፈጽሞ ችግር የሚፈጥር አይደለም ። ሕዝብዎ ባልሆነ አቅጣጫ ሊረዳው ይችላል ማለትን ስለ ሰማሁ መንግሥቴም ቢሆን የሚፈልገው አይሆንም ።

የቆንሲሉን የዳኝነት ሥልጣን በተመለከተ ነገሩ ያለው በእኛ እጅ ሳይሆን በእርስዎ እጅ ነው ። እንግሊዝ የምትፈልገው ሌላ ሳይሆን ዜጎቿ ፍትህና ያልተዛባ አስተዳደር እንዲያገኙ ብቻ ነው ።

ከግርማዊነትዎ ለመንግሥታችን የመንግሥትዎ አቋም ነው ብዬ የማምንበትን ቢገልጡ ፤ ይኸውም የተለየ የዳኝነት ሥልጣን ለመስጠት የማይቻልና ሕጉ ቀና በሆነበት በሀበሻ አገርም ይህን ማድረግ የማያስፈልግ መሆኑን ቢያስረዱ ለአሁኑ ይህ የሚበቃ ይመስለኛል ።

የጥቂት ሰዓቶች ንግግር ችግሩን ከሁለቱ ባንዱ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል ይመስለኛል ።

ከዚህ በኋላ ጥያቄው ንጉሡ በ1842 ዓ.ም. በእንግሊዝና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገውን ውል መቀበል አለመቀበል ሳይሆን ከታላቋ ብሪታንያ ጋር አዲስ ውል ለመዋዋል ፈቃደኛ መሆን አለመሆናቸው ነበር ። ለአዲሱ ድርድርም በቅድመ ሁኔታነት የቀረበ ነገር አልነበረም ። አዲስ ውል ለመደራደርም በቀድሞው ውል እንደሚገደዱ ለማመልከት የተጠቀሰ አንቀጽም አልነበረም ። እንዲያውም የቀረበው ሀሳብ “ የግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ ቢሆን ” የቀድሞው ውል ማሻሻያ ታክሎበት ለአዲሱ ውል በመነሻነት እንዲረዳ የሚያሳስብ ነበር ።

በዚህም የተነሳ ቆንሲሉ ያቀረበው የውል ሃሳብ እንግሊዝና ኢትዮጵያ በ1842 ከተፈራረሙት ውል ጋር ያልተያያዘ ራሱን የቻለ አዲስ ሀሳብ ነበር ። ካሜሮን አዲስ የውል ሃሳብ ማቅረቡ ውስጥ ውስጡን የቀድሞው ውል በንጉሡ ላይ ምንም የሕግ ግዴታ የማይጥል መሆኑንም መቀበሉን ያመለክታል ። ይህም ቆንሲሉ የሚወክለውን መንግሥት የቀድሞው የውል አቋም ያላላ ብቻ ሳይሆን ለቴዎድሮስም ከፍተኛ ድል ያጎናጸፈ ሁኔታ ነበር ። ሆኖም የክስተቶች ሂደት አዲሱ ጥረት ወደ ሰመረ ውጤት እንዲዘልቅ የሚረዳ አልሆኑም ።

እንግሊዝና ፈረንሳይ በክሪሚያ ጦርነት ክርስቲያን በሆነችው ሩሲያ ላይ አብረው እስላም የሆነችውን ቱርክን መርዳታቸው ቴዎድሮስ ከቱርክ ጋር ለነበ ራቸው አለመግባባት እነዚህ ሁለት ክርስቲያናት ኃያላን የአውሮፓ መንግሥ ታት ከጐኔ ይቆማሉ የሚል እምነታቸውን ጥያቄ ላይ ጥሎት ነበር ። ከዚያም ወዲህ በተከታታይ የተከሰቱ ሁኔታዎች ቴዎድሮስ በነዚህ መንግሥታት ላይ እም ነት እንዲያሳድሩ የሚረዱ አልነበሩም ። እንዲያውም ከ1856 በኋላ የእንግሊዝ ፖሊሲ. በኢትዮጵያ ኪሣራ ግብጽንና ቱርክን ለመጥቀም መዘመሙን የሚጠ ቁሙ ብዙ ምልክቶች ነበሩ ።

ይህም የዋለለ የእንግሊዝ የውጭ ፖሊሲ ከኢትዮጵያ ጋር የውል ግንኙነት ጨርሶ መመሥረት ለምን እንዳስፈለገ የእንግሊዝ ሹማምንቶች ሳይቀሩ ጥያቄ እንዲያነሱ አድርጓቸው ነበር ።

ሁኔታዎች በመዋለል ላይ በነበሩት በዚያ ያልታደለ ወቅት ነበር ቴዎድ ሮስ በካሜሮን በኩል ደብዳቤአቸውን ለእንግሊዝ ንግሥት የላኩት[30] ። ቆን ሲሉ የንጉሡን ደብዳቤ በኤደን ለንግሥቲቱ ልኮ በ1855 መጀመሪያ ላይ በሰሜን ኢትዮጵያና በግብጽ ግዛት ተዘዋውሮ ጉብኝት ለማድረግ ረጅም ጉዞውን ጀመረ ። ከጉዞው ሲመለስም ወደ ጐበኘው የኢትዮጵያ ጠረፍ አካባቢ የግብጽ ጦር የመ ገሰገሱ ጭምጭምታ በሰፈው በመናፈስ ላይ ነበር ።

ሆኖም ከተላከ ዘጠኝ ወሮች ያህል ቢያልፉትም ቴዎድሮስ በቆንሲል ካሜ ሮን በኩል ለንግሥቲቱ ለላኩት መልዕክት የመጣ መልስ አልነበረም ። ለቴዎ ድሮስም ሆነ ለካሜሮን አይታወቅ እንጂ እንግሊዝ ደብዳቤውን ችላ ለማለትና እንዲያውም መልስ ላለመስጠት ወስና ነበር[31] ።

በሐምሌ 1855 ዓ.ም. አካባቢ ካሜሮን ከጉብኝቱ ሲመለስ የመጠራጠሩና ክብራቸውም የመነካቱ ጉዳይ ለንጉሡ ከፉኛ ተሰምቷቸው ነበር ። በሰድብ ላይ ቁስል (በትር) እንደማከል ያህል ካሜሮን ከውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በተላከ ለት መመሪያ መነሻነት ወደ ምጽዋ ለመውረድ ይችል ዘንድ ንጉሡ እንዲያሰና ብቱት ጥያቄውን ውጥረት በተሞላበት በዚያ ወቅት አቀረበ ። በዚያ ወቅት ነበር ቴዎድሮስ በሚቀጥሉት ዓይነት ጥያቄዎች ካሜሮንን ያጣደፉት[32] ።

— ከሚሙኤል[33] ጋር በጐስ* ላይ ከተለያያችሁ በኋላ የት ነበርክ ?

— ከሱዳን ዳርቻ አውራጃዎች ፤

— ለምን ?

— ስለ ጥጥ ንግድ እንዲሁም ሌሎችን ጉዳዮችን ለማየት ፤

— እዚያ ማን ሂድ አለህ ?

— የእንግሊዝ መንግሥት ፤

— ከእንግሊዝ መንግሥት ለደብዳቤዬ መልስ አመጣህልኝ ?

— አላመጣሁም ፤

— ለምን አላመጣህም ?

---

* የዛሬው ከረን አካባቢ

— ምክንያቱም ከእንግሊዝ መንግሥት ያንን በተመለከተ የተላከልኝ ነገር ባለመኖሩ ፤

— አሁን ታዲያ ምን ልትሆን ወደኔ መጣህ ?

— ወደ ምጽዋ ለመመለስ ፈቃድ ልጠይቅ ፤

— ለምን ?

— በመንግሥቱ ስለታዘዝኩኝ ፤

— እና ያንተ ንግሥት ጠላቶቼን ቱርኮችን ሂደህ እንድትገበኝና ወደ ምጽዋ እንድትመለስ ትእዛዝ ይሰጡሃል ለኔ ደብዳቤ ግን የጨዋ መልስ መላክ አይችሉም ። መልስ እስካገኝ ከዚህ አትሄድም ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ንጉሡ ሀገሪቱን አንድ ለማድረግ እና የአስተዳደር ማሻሻያዎችን ለማስገባት የሚያደርጉት ጥረት ከግዛታቸው በአብዛኛው ክፍል ሁከትና ጦርነት ቀስቅሶ ነበር ። እነዚህ ሁሉ ባንድነት ተነባብረው ንጉሡን ሰላበሳ ጨዋቸው የኋላ ኋላ ወደ ከፋ ውጤት ያመሩ አንዳንድ ርምጃዎችን ለመውሰድ በቅተዋል ። በዚህ ረገድ ንጉሡ የወሰዱት አደገኛ ርምጃ ካሜሮንን ጨምሮ የውጭ አገር ዜጎች በሙሉ በታጋችነት እንዲያዙ ያስተላለፉት ትእዛዝ ነበር ። ቆንሲል ካሜሮን ከግብጽ ጋር ተመሳጥሯል ፤ ለንጉሡም ደብዳቤ ከንግሥቲቱ መልስ ሳያመጣ ቀርቷል በሚሉ ወንጀሎች ተይዞ ታህሣሥ 25 ቀን 1856 ዓ.ም. በእግረ ሙቅ ታስሯል ።

ከዚያ በኋላ አሳሳቢው ጥያቄ እንደገና ተለውጦ አዲስ ውል መዋዋል ሳይሆን ታጋቾችን ማስለቀቅ ሆኗል ።

በራሷ ጥፋት የተፈጠረውን ያንን ችግር ለማስወገድ ታላቋ ብሪታንያ ብዙ ጥረቶችን አድርጋለች ። ላለፈ ጥፋት ንስሐ እንደመግባት ያህል ንግሥቲቱ ለቴዎድሮስ ሁለት ደብዳቤዎችን ጽፈዋል ። ታጋቾችን የሚያስለቅቅ ውል ለመዋዋል በሆርሙዝ ራስም የሚመራ ሁለት አባላት የሚገኙበት የመልዕክተኞች ቡድን ተልኳል ። ቴዎድሮስ ታጋቾችን ለመልቀቅ ቢስማሙ አዲስ ውል ከቴዎድሮስ ጋር ለመዋዋል ታላቋ ብሪታንያ ፈቃደኛ መሆኗን ገልጣለች ። ነገር ግን እንግሊዝ ያሳየችው የአቋም ማላላት ዘግይቶ በመምጣቱ ይሆን ፤ ወይም እስከሚፈልጉት ድረስ አለመሄድ የአጼ ቴዎድሮስን የጠነከረ አቋም ሊያስለውጥ አልቻለም ።

በዚህም የተነሳ ራሳምና ጓደኞቹ ሳይቀሩ እንዲያስፈቱ የተላኩትን እሥረኞች ዕድል መቋደስ እጣ ፋንታቸው ሆነ ። የሚያስገርመው ቴዎድሮስ ባንድ አጋጣሚ ታጋቾች ካሜሮንም ጭምር ለፈጸሙት ወንጀል ተከስሰው በፍትሐ ነገሥቱ ቃል መሰረት ፍርድ ይሰጥባቸዋል በማለት መግለጣቸው ነው ። [34] እንግዲህ የእንግሊዝን ዜጎች ከሀበሻ ሕግና የዳኝነት ሥርዓት ውጭ እንዲደረግ ታስቦ የተረቀቀው ውል ከሀበሻ ሕግ በላይ ነው የተባለውን ቆንሲል እንኳ ማዳን ሳይችል ቀርቷል* ። በመሆኑም ካሜሮን ወደ ሀገሩ ያዘገመው በቆንሲልነቱ የሚገባውን ክብር ማግኘት ቀርቶ በ1842 ዓ.ም. በተደረገው ውል ላይ የተመለከቱትን የንግድና የዳኝነት ሥልጣን ለሀገሩ ማስከበር ተስኖት ስለነበር የአርሱም ተልዕኮ ከፕላውዴን ባልተሻለ ሁኔታ የተቀዋጣ አልነበረም ።

---

* የውሉን አንቀጽ 3 ይመለከቷል ።

እንደእውነቱ ከሆነ ታላቋ ብሪታንያ ታጋቾችን በማስመልከት ለቴዎድሮስ ባስተላለፈችው መልዕክት ላይ በ1842 ዓ.ም. የተደረገውን ውል አንቀጾች ተጠቃሽ አላደረገችም ። ቆንሲሉንና ፤ የእንግሊዝን ዜጎች በታጋችነት መያዝ የውሉን አንቀጽ በግልጽ መጣስ ስለመሆኑ እንግሊዞች ለቴዎድሮስ ለመግለጥ አልሞከሩም ። ታጋቾቹን ለማስለቀቅ በመጨረሻም የወሰዱትን ርምጃ ተገቢነት ለማሳየት ውሉን በድጋፍነት አልጠቀሱም ። ንግሥቲቱ ለቴዎድሮስ የላኩዋቸው ሁለት ደብዳቤዎችም ስለውሉ በግልጽ የሚያነሱት ነገር የለም ። በማማለድ መንፈስ የተጻፈው የንግሥቲቱ የመጀመሪያ ደብዳቤ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ወዳጅነት ሲሉ ታጋቾቹን እንዲለቁ የሚማጸን ነው ።

አግባብ ያለው የደብዳቤው ክፍልም እንዲህ ይላል ። [35] ግርማዊነትዎ በሐቅ የኛ ወዳጅ ስለመሆንዎ እና በመካከላችንም ያለው ወዳጅነትና መተሰብለዘለቄታው ጸንቶ እንዲቆይ የሚሹ መሆንዎን አገልጋዮችንን ካሜሮንን . . ከቤተ መንግሥትዎ እንዲሰናበት ከማድረግ የተሻለ ማስረጃ ሊሰጡ አይችሉም ።

መስከረም 24 ፡ 1859 ዓ.ም. የንግሥቲቱ ሁለተኛውና የመጨረሻ ደብዳቤ ሲጻፍ የነገሮች ሂደት ወደ ባሰ አዘቅት አሽቆልቁሎ ነበር ።

በዚህም የተነሳ ቴዎድሮስ ታጋቾችን ለመፍታት የገቡትን ቃል ሁሉ ችላ ብለው የውጭ አገር ዜጎች በሙሉ ራሳምና ጓደኞቹ ጭምር ተይዘው እንዲታሰሩ አዘዙ ። ንግሥቲቱ በበኩላቸው ለጥያቄአቸው ሕጋዊና ሥነ ምግባራዊ ምክንያቶችን ጠቅሰው እሥረኞቹ እንዲለቀቁ አሳስበዋል ። ማግባባትና ከበሬታን የተላበሰ ወቀሳን አጣምሮ የያዘው የዚያ ደብዳቤ ቃል በከፊል ሲታይ እንደሚከተለው ነው ። [36]

> ነገሥታት የገቡትን ቃል በጥንቃቄ መጠበቅ ያለባቸው መሆኑን ግርማዊነትዎ ልብ ሊያደርገው ይገባል ፤ እንደራሳም ያሉ አምባሳደሮች ሰውነትና የተከታዮቻቸውም ጭምር ሰልጥነናል በሚሉ አገሮች ሁሉ የማይደፈር ነው ፤ በነገሥታት መካከል ያለዎትን የክብር ሥፍራ ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆንዎን ለዓለም እንዲያሳዩ ለግርማዊነትዎ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን ።

የፖለቲካ ሰዎች ችላ ያሉት ውል በጦር መኮንኖችም ቢሆን ነፍስ ሊዘራ አልቻለም ። ናፒር “ ይድረስ ለቴዎድሮስ ንጉሠ ሀባሻ ” በማለት አስቀድሞ በጻፈው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤውም ሆነ “ ለሀበሻ ገዢዎች ፤ ለአድባራት አለቆች ፤ ለሃይማኖት መሪዎችና ለሀበሻ ሕዝብ ” [37] በማለት ባስነገረው አዋጅ ስለ ውሉ የጠቀሰው አንድም ነገር የለም ።

የታጋቶቹ ጉዳይ ሚያዝያ 2 ቀን 1860 ዓ.ም. በቴዎድሮስ ወታደሮችና በጀኔራል ናፒር መሪነት በዘመተው ወራሪ የእንግሊዝ ጦር መካከል በተደረገው ዝነኛው የመቅደላ ጦርነት* እልባት አግኝቷል ። የናፒር ዘመቻ የክስተቶችን ሂደት ተከትሎ ሊመጣ የሚችል ጉዳይ በመሆኑ ቴዎድሮስ ያልጠበቁት እንግዳ ነገር ሊሆንባቸው የማይችል ነው ።

* ፊልድ ማርሻል ሮበርት ናፒር ስለክብሩ በሎንደን ኩዊንስ ጌት የመታሰቢያ ሐውልት ቆሞለታል ። ከግርጌውም “ የመቅደላው ሎርድ ናፒር ” ተብሎ ተጽፎበታል ።

በወቅቱ የቴዎድሮስ ኃይልም ሆነ የውጊያ ብቃት የሚገኘው እጅግ በተዳከመ ሁኔታ ነበር ። የነበራቸው ኃይል በቁጥርም ሆነ በጥራት ከቦምቤይ ተነስቶረጅሙን መንገድ ተጉዞ ለውጊያ ታጥቆ ከዘመተው ወራሪ ጦር ጋር ሲነጻጸር ቁጥር ሊገባ ፈጽሞ የማይችል ነው ። በነገሮች መጫን በዚህ ዓይነት ውጥረት ላይ ይገኙ የነበሩት ቴዎድሮስ ያላቸው ምርጫ ከናፒር ሠራዊት ጋር በጦር ሜዳ መገናኘት ወይም ከናፒር ጋር ተገናኝቶ ጦርነቱን ማስቀረት ብቻ ነበር ። ከነዚህም የመጀመሪያውን ምርጫቸው በማድረግ ተጽእኖ ባልተለየው ሰላማዊ መንገድ ቀስ በቀስ አገርንና ራስን አሳልፎ ከመስጠት ይልቅ "በቀጥታ ከጦሩ ጋር መፋለምን" የሚመርጡ መሆናቸውን በተግባር አሳይተዋል [38] ።

እንደሚገመተው በጦርነቱ ድል የተነሱት ቴዎድሮስ ናቸው ። ሆኖም ድል የተመቱ ቢሆንም ድል አድራጊዎች በታላቅ ቀናኢነት የሚመለከቱትን ፍላጐታቸውን ጠላቶቻቸው እንዲቀበሉ የማስገደድ መብት ተግባራዊ ለማድረግ እንግሊዞች ይችሉ ዘንድ ቴዎድሮስ በሕይወት አልተያዙላቸውም ።

ነገሩን መለስ ብለን ብንቃኘው እንግሊዞች የኢትዮጵያን ክብርና ሉዐላዊነት የሚነካ የውል ሁኔታ በተጽእኖ ከማስፈረም የሚመለሱ አልነበሩም ። ነገር ግን ቴዎድሮስ ለወራሪው በተሸናፊነት እጅ ከመስጠት ይልቅ ሞትን ስለመረጡ ሚያዝያ 5 ቀን 1860 ዓ.ም. ወደ ማታ በገዛ እጃቸው ሕይወታቸውን አሳልፈዋል ።

<u>መደምደሚያ</u>

ሆኖም ቴዎድሮስ የጦርነቱ ብቸኛ ተጐጅ አልነበሩም ፣ ሞታቸውም በከንቱ አልነበረም ። ቁርጠኛ አቋማቸው ታላቋ ብሪታንያ በ17943 በቅሎዎችና አጋሰሶች በ2538 ፈረሶች በ1759 አህዮች በ8975 በሮች ፤ በ5735 ግመሎች በ44 ዝሆኖች የሚረዱ 42 000 ሰዎችን እንድታሰልፍ አስገድዷታል። ለዚህም ዘጠኝ ሚሊዮን ፓውንድ የወጣ ሲሆን ፣ ይህም ለጦርነቱ ከተመደበው በአምስት ሚሊዮን ፓውንድ ከፍ ያለ ነው ። ይህም ሁሉ ኃይል የተሰለፈው ፤ ይህን ያህል ገንዘብም የፈሰሰው ከ7000 ሰው የማይበልጠውን የቴዎድሮስ ጦር ለመግጠም ነበር [39] ። በዚህም ትክክለኛ የሆነ ውል ለመዋዋል የሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች የጋራ ፈቃድና ሙሉ ፍላጐት አስፈላጊ ስለመሆኑ ቴዎድሮስ በተጨባጭ እንግሊዞች እንዲያጤኑት አድርገዋል ። እንደዚሁም ሀበሻ ብሪታንያን ጨምሮ ከአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት ጋር በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲኖራት ያላቸውን ጽኑ ፍላጐት አጉልተው ለማሳየት ችለዋል ።

ባጭሩ ሞታቸው ጽኑ አቋማቸውንና እንቢተኛነታቸውን ባንድነት አጣምሮ የሚያሳይ ነው ። መልዕክቱም ከእንግሊዞች የተሰወረ አልነበረም ።

ስለዚህ ጦርነቱ እንዳበቃ ናፒር ሲጽፍ የሚከተለውን ብሎ ነበር ።

> ከሀበሻ መሪዎች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር የእንግሊዝ መንግሥት በአፍሪካ ውስጥ ቆንሲል ላለማስቀመጥ ወስኗል [40] ።

ከዛም ሩቤንስን በትክክል እንደገለጠው " ቆንስሎቻቸው በምድር ሀበሻ ሰንደቅ ዓላማቸውን ለማውለብለብ ላደረጉት ጥረት የከፈሉትን ከፍተኛ መስዋዕትነት በማጤንና እንደዚህ ያለ ሁኔታ ለወደፊት እንዳይከሰት በማሰብ " እንግሊዞች በሀበሻና በጠረፎቿ የዘረጉዋቸውን የቆንሲል መረቦች ወዲያውኑ እንዳነሱ እንገነዘባለን ። [41]

የቴዎድሮስ ነገር በዚሁ አክትሟል ። ከርሳቸው ሞት ጋርም የ1842 ዓ.ም. ውልና እንግሊዞች በኢትዮጵያ የነበራቸው ዕቅድ ገብአተ መሬት ተፈጽሟል ። በዚሁ እንግሊዞች ለሃያ ዓመታት ያህል ሲያራምዱት የነበረው የዲፕሎ ማሲ ያዊ እንቅስቃሴ በውድቀት ተደምድሟል ። ሆኖም ውድቀቱ እንግሊዞቹን ለዘለ ዓለም አስመርሮ ቆንስላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የዳኝነት ሥልጣን እንዲኖረው እንዳይፈልጉ የሚያደረግ አልነበረም ።

በዚህም የተነሳ ከ40 ዓመት በኋላ በ1900 ዓ.ም. በተፈረመው የክሎቢኪ ውሲኪ ውል አማካይነት ታላቋ ብሪታንያ ይህን ዓይነት መብት ብታስከብርም ፤ ይህን ማድረግ የቻለችው በፈረንሳይ[42] ጥላ ሥር ታካ በመግባትና በ1842 ዓ.ም. ውል ላይ ከተመለከተው እጅግ የደከመና የለዘበ የውል ሁኔታዎችን ተቀብላ ነው ።

## የግርጌ ማስታወሻ ።

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ የጠቅላይ ፍ/ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ። ኤል ኤል ቢ የሕግ ፋኩልቲ አአዩ (ቀኃዩ)፤ ኤል ኤል ኤም ማንቸስተር ዩኒቨርሲቲ ። በግልጽ ካልተመለከተ ጊዜው የተገለጸው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው ።

1. ሲ. ኤች አሌክሳንድሮዊች ፤ " አን ኢንትሮዳክሽን ቱ ዘ ሂስትሪ ኦፍ ዘሎው ኦፍ ኔሽንስ ኢን ዘ ኢስት እንዲስ " ኦክስፎርድ (1967) ገጽ 97—101 ።

. " የክሎቢክዊስኪ ውል በመባል የሚታወቀው " የ 1900 ዓ ም የፈረንሣይና የኢትዮጵያ ውል ዜጐችን የመዳኘት ሥልጣን ሰጥቶ የነበረው ኢትዮጵያ ለሚገኘው የፈረንሣይ ቆንሲል ብቻ ነው ። በ1920ዎቹ ግን ሀገሮቻቸው ከኢትዮጵያ ጋር የገቡትን " ይበልጥ ተጠቃሚ አገር " የሚለውን የውል ሐረግ መሠረት በማድረግ ከ10 የማያንሱ አገሮች የቆንሲል ፍርድ ቤቶችን አቋቁመው ነበር ።

3. ጂ ኤል ብሪየርሊ ዘ ሎው ኦፍ ኔሽንስ (ኦክስፎርድ — 6ኛ እትም እ. ኤ. አ. 1967) ገጽ 173—174።

4. ደብልዩ ሲ ፕላውዲን ትራቭል ኤን አቢሲኒያ ኤንድ ዘ ጋላ ካንትሪ (ሎንደን እ. ኤ. አ. 1868) ገጽ 7

5. ፎርይን ኦፊስ (አፍአ 401) 1 ገጽ 7—10 በሩቢንሰን እንደተጠቀሰው ዘ ሰርቫይቫል ኦፍ ኢትዮጵያን ኢንዲፔንደንስ ኖርዊች (እ. ኤ. አ. 1978) ገጽ 20 ።

6. ኤፍኦ 401( ገጽ 1 — 2 በሩቢንሰን እንደተጠቀሰው ገጽ 129 ።

7. ቻርለስ ቢክ ፤ ዘ ብሪትሽ ካፕቲቭ ኢን አቢሲንያ ። ( ሎንግ ማንስ ሎንደን እ. ኤ. አ. 1867) ገጽ 19።

8. በሩቢንሰን እንደተጠቀሰው ገጽ 121 ።

9. ጆርጅ አንሰሌይ ቮየጅስ ኤንድ ትራቭልስ — ቱ ኢንዲያ . . አቢሲንያ (ለንደን እ.ኤ.አ. 1809) ቮልዩም 3 ገጽ 263—264 ።

10. በቢክ እንደተጠቀሰው ገጽ 55—56 ።

11. ሩቢንሰን ገጽ 131 ።

12. ፕላውዴን ገጽ 420 — 421 ።

13. በሩቢንሰን እንደተጠቀሰው ገጽ 137 ።

14. የውሉን የእንግሊዝኛ ጽሑፍ ለማግኘት ክላይቭ ፓሪ ዘ ኮንሶሊዴትድ ትርቲ ሴሪስ ቦልዩም 103 ገጽ 299 — 303 ፤

15. ከዚያው ቮልዩም 92 ገጽ 272—276 ።

16. ጠንቀኛ መባሉ ምክንያቱም የውጫሌ ውል ተብሎ በሚታወቀውና የ1881 ዓ.ም. የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ውል አንቀጽ 17 ላይ የተፈጠረው አለመግባባት ነበር ለዝነኛው የአድዋ ጦርነት መንገድ ከፋች የነበረው ።

17. በእርግጥ በቀረበው ገጸ በረከት የተደሰቱ መሆናቸውን ለመግለጽ ራስ አሊ ለፕላውዲን ሁለት መንደሮች ሰጥተው ነበር ። ፕላውዴን ገጽ 396—399 ።

18. የሰኔ 17 1847 ዓ ም ዘገባ በቢክስ እንደተጠቀሰው ፤ ገጽ 48 ።

19. ከዚያው ።

20. ይህንንም ከፕላውዲን ትረካ መረዳት ይቻላል። " በሁለቱ የውል ቅጂዎች በማህተማቸው ካተሙ በኋላ የራሳቸውን ድርሻ ለሚያቀርቡት አንድ ደብተራ ሰጥተው ደብረ ታቦር ወስዶ እንዲቀልፍበት አዘዘ ። የራስ ቤት በ1846 ዓ ም በደጃች ካሣ የተዘረፈና የተቃጠለ ስለሆነ ውሉ ስካሁን ሳይጠፋ አይቀርም ። " ፕላውዲን ገጽ 421 ።

21. በቢክ የተጠቀሰ ገጽ 52 ።

22. " አባ ሰላማ (ከእስክንድርያ የመጡት ጳጳስ) በኢትዮጵያ የነበረችውን የሮማ ቤት ክርስቲያንና ደጋፊዋን የፈረንሳይን መንግሥት ጥቅም አጥብቀው የሚጸረሩ ፤ ባንጻሩ ደግሞ የፕሮቴስታንት ወገን ጥብቅ ደጋፊ በመሆን የእንግሊዝን ጥቅም የሚያራምዱ ስለነበር ለዚሁ ወሮታ ድርጐ ተቆርጦላቸው ከፕላውዲንና እርሱም ከሞተ በኋላ ምጽዋ ከነበረው ወኪሉ ይቀበሉ እንደ ነበር ቻርለስ ቢክ ጽፎአል ። ገጽ 16—17 ።

23. የፕላውዴን የሰኔ 17 ፥ 1847 ዓ. ም. ዘገባ ፤ በቢክ እንደተጠቀሰው ገጽ 37 ።

24. ከዚያው ገጽ 35—38 ።

25. ከዚያው ገጽ 43 ።

26. ከዚያው ገጽ 54—55 ።

27. ከዚያው ገጽ 98 ።

28. ከዚያው ገጽ 67—68 ።

29. ቤክ የደብዳቤውን ቅጂ ከገጽ 312 — 316 አስፍሮታል ፡፡

30. በ1855 ዓ ም ጥቅምት 19 ጐጃም ባይባባ ከተማ የተጻፈው ደብዳቤ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ግርማ ሥላሴ አስፋው በጻፉት የኢትዮጵያ ንጉሥ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቪክቶሪያና ለልዩ መልዕክተኛው በአማርኛ የጻፉአቸውን ደብዳቤዎች ፣ መጽሐፍ ላይ ገጽ 3—3 ይገኛል ፡፡

(ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ እ. ኤ. አ. 1979)

31. የንጉሡ ደብዳቤ በየካቲት 1855 ዓ ም ለውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ደርሶ በሶስተኛው ወሩ ለሕንድ ጉዳይ ጽ/ቤት ተልኮ ነበር ፡፡ እዚያም ለአንድ ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ ምንም አስተያየት ሳይታከል በት ግንቦት 3 ቀን 1856 ዓ ም ተመልሶ ለውጭ ጉዳይ መ/ቤት ተልኳል ፡፡ ግርማ ሥላሴና ሌሎች ገጽ ፤ 12

32. ቤክ ገጽ 93 — 94 ፡፡

33. ሳሙኤል የተባለው ከካሜሮን ጋር እስከ ምጽዋ ድረስ አብሮ የሔደው ከንጉሡ ትርጁማኖች ውስጥ አንዱ ነበኦር ፡፡

34. ከዚያው ገጽ 235 ፡፡ ከዚህ ትንሽ ቀደም ብሎ እሥረኞቹ በጊዜያዊነት ተለቀው ለራሳም ከተሰጡ በኋላ በራስም ድንኳን ውስጥ በተካሄደው ችሎት ላይ የተደረገውን ዋልድማየር እንዲህ ሲል ገልጦታል ፡፡

ባለፈው ሳምንት እኛ የጋፋቶቹ ማለትም ፍላድና ወንድሞቻችን እንደዚሁም የተፈቱት እሥረኞች ጭምር በተገኘንበት በንጉሡ ትእዛዝ በራሳም ድንኳን ውስጥ ጉባኤ ነገር መሰል አድርገን ነበር ፡፡ ንጉሡ በካፒቴን ካሜሮን ፤ በባርዲል ፤ እና በሚሲዮናውያኑ በእነ ሽተርን እና ሮዜንታል ላይ የነበራቸው ክስ በጽሑፍ ቀርቦ ተሰምቷል ፡፡ ተከሳሾቹም ጥፋተኝነታቸውን በጉባኤው ፊት አምነው ተቀብለዋል ፡፡ በተለይ ሚስተር ሽተርን ሁሉንም ወክሎ “ ንጉሡን በድለናል ለዚህ የሚገባንን ቅጣት አግኝተናል እግዚአብሔር ለግርማዊነታቸው ረጅም ዕድሜ ፤ ለአገራቸው ብልጽግና ለጠላቶቻቸው ደግሞ ሽንፈትን እንዲሰጥ እንጸልያለን ፡፡ ” በማለት ተናግሯል ፡፡ በስብሰባው ላይ ቴዎድሮስ አልተገኙም ፡፡ በቤክ የተጠቀሰ ገጽ 210 — 211 ፡፡

35. አለን ሞርሄድ ዘ ብሉ ናይል (1980 እ. ኤ. አ.) ገጽ 218 ፡፡

36. ከዚያው ገጽ 232 ፡፡

37. ከዚያው ገጽ 244—245 ፡፡

38. ከሁለቱ ሠራዊቶቻቸው የሚሬ ግጭት በኋላ ጉዳዩን በሰላም ለመጨረስ ቴዎድሮስ እጃቸውን እንዲሰጡ ናፒር ጥያቄ ሲያቀርብላቸው እንዲህ ሲሉ ነበር የመለሱለት ፤

“ ታላቅና ጠንካራ ሰዎችን እንደ ሕጻናት በክንዱ ሲጫወትባቸው የነበረ ሰው በሌሎች እጅ ወድቆ እንዲጫወቱበት ፍጹም በጇ አይልም ፡፡ ” በሩቢንሰን የተጠቀሰ ገጽ 265

39. ሩቢንሰን ገጽ 257 ፡፡

40. በሩቢንሰን የተጠቀሰ ገጽ 273 ፡፡

41. ከዚያው

42. ከላይ የተጠቀሰውን ማስታወሻ ቁ. 1 ይመለከቷል ፡፡ የውሉን ጽሑፍ በሚመለከት ኤ. ጂንጉልደ ዱፕሪይ ደ ለ ኢንቬዚዮን አላሲቤሬሲዮን ደ ለ ኢቶዮፒ ቦልዩም 2 ፤ ፓሪስ 1955 (ገጽ 426—428 ይመለከቷል ፡፡

## የአጼ ቴዎድሮስ ደብዳቤዎች *

ዛቲ ጦማር ዘተፈነወት እምኀበ ንጉሠ ነገሥት
ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ ።
ትብጻሕ ኀበ ንግሥተ እንግሊዝ ብክቶርያ ።
እንዴት ነዎ ደኅና ነዎን ።
እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ ።
አቶ ቡላውዲንን የእርስዎ መላክተኛ ነው ብዬ ።
በፍቅር በወዳጅነት ተቀብዬው አለሁ ።
እስተ ዛሬ ድረስ ያለ መላኬ ባላርፍ ባይረጋልኝ ነው ።
አሁንም እርስዎም የክርስቶስ ልጅ ነዎ ።
እኔም የክርስቶስ ልጅ ነኝ ።
ስለክርስቶስ ፍቅር ወዳጅነት ፈልጌአለሁ ።
አሁንም ክርስቶስ ደሥ ቢአሠኝኝ ።
ሥንረጋ ደሥታየን ሁሉ ሺማግሌ ሰው ጨምሬ ።
ካቶ ቡላውዲን ጋር እልክ አለሁ አብሮ ደስ እንዲለን ።

( ማሃሉ ላይ ዘውድ የሜነ አንበሳ ፡ ዙሪያውን ከታች " ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ " የሚል ከላይ የአረብኛ ጽሕፈት ያለበት ማኅተም አለ ፡ አዘጋጅ ። )

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ
ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ ። ከአቶ ቦረኒ ።
እንዴት ሠነበትህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ ። የምሥራች በእግዚአብሔር ኃይል ቀናኝ ። ወዳጆቼን ቡላዲንን ዮሐንስን የገደሉን ሠዎች ፈጀኋቸው በእግዚአብሔር ኃይል ከሜት በቀር ከሠልፍ ያገኘሁትን ሁሉ ፈጀሁት አንድ አልተውሁም ። ወዲያው ተከታትዬ ተሻግሬ ሴባ ንጉሜን በእግዚአብሔር ኃይል ከነሠራዊቱ ፈጀሁት አኩስም ከሜዳው ላይ ። አንተንም ቶሎ ናልኝ ። ከዕንግሊዝ ንግሥት ከወዳጀ እግዚአብሔርን ያደረገልኝን የደሥታየን ወሬ የምልክ ሠው የምሠድ ነኝና ቶሎ ናልኝ ይዘህልኝ የምትሄድ ነህና ። የሊቀ መኳስ ዮሐንስን ። የአቶ ቡላዲንን ሠዎች እስታሁን ያቆየኋቸው ከኔ ሰው ካንተ ጋራ ይሄዱ ብየ ነው ።

(ማኅተም እላይ እንደተገለጸው አለ ፤ አዘጋጅ ። )

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ
ባንድነት በሶስትነት እግዚአብሔር መርጦ ያነገሰው ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ ይድረስ ። ከዕንግሊዝ ነገሥት ቢክቶሪያ ። እንዴት አሉ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ ። እስተ ዛሬ ድረስ አባቶች ነገሥታቱ ፈጣሪአችንን ቢበድሉት መንግሥታቸውን . . . እሣልፎ ሰጥቶባቸው ነበረ ዛሬ ግን እኔ ከተወለድሁ ፈጣሪየ ካመድ አንስቶ ኃይል ሰጥቶ ባባቶች መንግሥት አቆመኝ በእግዚአብሔር ኃይል . . . አስለቀቅኋቸው ቱርኮች ግን ያባቴን መሬት ልቀቁ ብላቸው እምቢ ብለውኝ

* እነዚህ ደብዳቤዎች ከዋናው መጣጥፍ ጋር እንዲወጡ ያረግ ነው ለተተቸው ሁኔታ መሠረታዊ ሰነድ ናቸው በሚል ነው ። (አዘጋጅ)

በእግዚአብሔር ኃይል ይኸው ልታገል ነኝ። እነአቶ ቡላዲን እነሊቀመኳስ ዮሐንስ የክርስቲያን ንጉሥ ታላቅ ሰው ክርስቲያን የሚወዱ አሉ እናስተዋውቅህአለን እያሉኝ እጅግ እወዳቸው ነበረ የርስዎን ወዳጅነት ያገኘሁ እየመሰለኝ ። ሞት አይቀርምና የጠሉኝ ሰዎች እኔን ይክፉው ሲሉ ገደሉአቸው እኔም በእግዚአ ብሔር ኃይል ደመኞችን ፩ ሳልተው ፈጀኋቸው የገዛ ዘመዶቼን ። በእግዚአብሔር ኃይል የርስዎን ዝምድና ሥፈልግ ። ቱርኮች ከባህር ላይ ሁነው መልክተኛየን አናሳልፍም ብለው ቸግሮኝ ሳለ ቆንስል ኬሜሮን መጣልኝ ወረቀትና የፍቅር በረከት ይዞ ። በእግዚአብሔር ኃይል እጅግ ደስ አለኝ ደህንነትዎንና ፍቅር ዎን ብስማ የሠደዱልኝንም የፍቅር በረከት ተቀበልሁ እግዚ አብሔር ይሥጥልኝ ። አሁንም መልክተኛየን ቆንስል ኬሜሮን ጋር የፍቅር በረከት ይዞ እንዳልሰደው ቱርኮች በባህር ላይ የማ ያስተላለፉልኝ ሆነ አሁንም እንዲህ ባለ ስፍራ እከሌ ይቀበለው ብለው ይላኩብኝ ። ምላሹን ቆንስል ኬሜሮን ይዞልኝ ይምጣ ። እናንተም ተገፉልኝ . . . ።

ተጻፈ በ፲፱፻፳፰ ዘመን በሉቃስ ?

በወርኃ ጥቅምት በ፳ ቀን ጐጃም በይባባ ከተማ

( ማኅተም የለም ። አዘጋጅ ። )

## የወዳጅነትና ፣ የንግድ ውል

## በእንግሊዝ ንግሥትና በሐበሽ ንጉሥ መካከል

በንግድ እጅግ ሀብት እጅግ ገንዘብ የሚገኝ ከሆነ ስለዚያ አገሮች በወዳጅነት በፍቅር የታሰሩ ። የውል ማለቂያ የዘለዓለም ወዳጅነትና ንግድ በንግሥት እንግሊዝና በሐበሽ ንጉሥ መካከል በማድረግ ሁለቱ አገሮች እጅግ የሚጠቀሙ ስለሆኑ ካሁን ቀድሞ ስለተፈለገ በሁለቱ ነገሥታቶች ። የሁለቱ አገሮች ንግድ ውል እንደምን እንደምን የሚሆን እንዲጻፍ የሚገባ እንደሆነ ስለዚህ የሚከተለውን ውል ሁሉ ተነግሮና ተደርጎ ባቶ ፑላውዱን ኩንስል ንግሥት እንግሊዝ በሐበሽ ይህን ውል ለማሰር ታዘው በንግሥት እንግሊዝና በሐበሽ ንጉሥ መሀል ። ውል ፊተኛ ብርቱ ልብ ለልብ የሚሆን የሚሰነብት ፍቅር በንጉሠ ሐበሻና ቀጥሎ በሚነግሥ በእንግሊዝ ንግሥት ፊት ጦሪያና ቀጥሎ በሚነግሥ ማኸል እንዲኖር ።

### ሁለተኛ ።

የሁለቱ አገር ያሁን ቀደም ወዳጅነት እንዲጠና እንዲጨመር የሐበሽ ነገሥታትና ቀጥለው የሚነግሡ ከንግሥት እንግሊዝና ቀጥሎ ከሚነግሥ የተላከ ቢሆን ኩንስልም ቢሆን እንዲቀበሉ እንዲጠብቁ ወግም እያጥፉባቸው ያክብርዋቸው ።

### ሶስተኛ ።

እንዲህ ደግሞ ንግሥት እንግሊዝና ቀጥሎም የሚነግሥ ከሐበሻ ንጉሥ ቀጥሎም ከሚነግሥ የተላከ ቢሆን ሹምም ቢሆን ይቀበላሉ ይጠብቃሉ እንደዚህ ደግሞ ወግ እያጠፉባቸውም ያክብርዋቸዋል ።

### አራተኛ ።

ንጉሠ ሐበሽ ውል ይሰር ሊሰጥ ለዜጎች ለእንግሊዝ ንግሥት ለቃቸውና ለንዳቸው ቸርነትን ሁሉ ማክበርን ሁሉ ነጣነትን ሁሉ ወይም በቀረጥ ወይም በግብር ወይም በሌላ ነገር ከዚህ በፊት ሰጥቶ እንግዲህም የሚሰጥ ቢሆን ።

### አምስተኛ ።

የእንግሊዝ ዜጎች ወዲህ ወደሐበሻ የሚያገቡት ዕቃ ሲገባ ቀረጡ አምስት ከመቶ ይጣልና ይቀበል ንጉሠ ሐበሽና ቀጥሎ የሚነግሥ በሐበሽም ቢሆን ቢሸጥ ወዲያ ከሌላ አገር አልፎም ቢሸጥ ።

### ስድስተኛ ።

ይህ አምስት በመቶ የተጣለው ገቢ ቀረጥ በጎንደር ገቢያ ዕቃ እንደሚሸጥ በወራቱ ይገምግምና ይሰጥ ይህን አምስት በመቶ የተጣለውን ግምግሙንም ቢሆን ዕቃውንም ቢሆን ነጋዴው እንደወደደ ይስጥ ።

### ሰባተኛ

ይህን አምስት በመቶ የተባለን ቀረጥ በሚገባ ሰጥቶ የሚያገባው ነጋዴ ዕቃውን በስፍራው ሁሉ በግዛተ አበሽ በፈቀደው እንዲሸጥ ዕቃው ለመውጣቱ ትእዛዝ ሳይፈልግ ሳይከለከል ሳይቸገር ሌላ ገቢ ቀረጥ ሳይጣልበት ከገገፑ ላይ ሁለተኛ ቀረጥ እንዳይጣልበትና እምያገባው ነጋዴ ያን ዕቃ ከሌላው ስፍራ ከሌላ አገር በወደደው ይውሰድ ለመውሰዱ ትእዛዝ ሳይፈልግ ሳይከለከል ሳይቸገር ሳይበደል ሌላ ምንም ቀረጥ ሳይከፍል ።

ስምንተኛ ።

የእንግሊዝ ነጋዶች የሚሹትን ሁሉ ዕቃ በፈቀዳቸው እንዲገዙ በግዛተ ሐበሽ ያም ዕቃ የሐበሽም ቢሆን ወይም ከሌላ የመጣ ቢሆን እኚያ ነጋዶች በፈቀዳቸው ያን ዕቃ ወስደው ምንም ቀረጥ እንዳይከፍሉ ።

ዘጠነኛ ።

የሐበሽ ንጉሥ ዜጎች በንግሥት እንግሊዝ አገር በሌላ አገር የተወደዱ ዜጎች የሚያገኙትን ቸርነት ሁሉ የሐበሽ ንጉሥ ዜጎች ያገኛሉ ከሐበሽ የሚመጣ ዕቃ ከእንግሊዝ ንግሥት የሚገባ ዕቃ ከሌላ አገር የሚመጣው ዕቃ ከሚቀረጠው የበለጠ አይቀረጥም ።

አስረኛ ።

እኛ በኛ ንግድ በሐበሽ ዜጎች በሐበሽ አጠገም ያሉ አገሮች ሁሉና በእንግሊዝ ዜጎች ማኸል ይሁንና ይደረግ ።

አስረኃንደኛ ።

የሐበሽ ንጉሥና ተከትሎ የሚነግሠው የሌላውን የሩቁን አገር ነገዶች ያባብሉ ዕቃቸውን በሐበሻ ግዛት እንዲያመጡ በዚያ ንግድ እንዲያመጡ በዚያ ንግድ እንዲበዛ እንዲጨመር በሐበሻና በእንግሊዝ መካከል ።

አስራሁለተኛ ።

ባንድ እኩል ደግሞ እንግዲህ ይህን አይተው ንግሥት እንግሊዝና ተከትለው የሚነግሡ የእንግሊዝ ነጋዶች በሐበሽ የተፈለገውን ሁሉ ዕቃ እንዲያመጡ ያደርጋሉ ።

አስራዕስተኛ ።

ለነጋዶችና ለከብታቸው ጤና ማግኘት የሐበሽ ንጉሥና ተከትለው የሚነግሡ የእንግሊዝ ንግሥትና ተከትለው የሚነግሡ እንደጉልበታቸው ይጠብቃሉ መንገድ ያስመቻሉ ከባሕር እስከ ሐበሽ ድረስ ።

አስራራተኛ ።

የሁለት አገር ዜጎች መገናኛቸው እንዲገፉ እንዲጨመር የሐበሽ ንጉሥ ለርሳቸውና ተከትሎ ለሚነግሥ ውል ያደርጋሉ የእንግሊዝ እንግዶች ክፋትና መከልከል እንዳያገኛቸው በሐበሻም ግዛት ተቀምጠው ቢሆኑ ወይም ወደሌላ አገር ለማየት ሲያልፉ ቢሆኑ ሰውነታቸውና ከብታቸው በውል እንዲጠበቅ ።

አስራአምስተኛው ።

የኒህ እንግዶች ለመሸጥ ያላመጡት ዕቃቸው ምን ምን እንዳይቀረጥ በማናቸውም ምክንያት ሁኖ ገንዘባቸው እንዳይነካባቸው ።

አስራስድስተኛ ።

የሐበሽ ንጉሥ ዜጎች ምንምን ክልከላ ምን ምን መቸገር አያገኛቸውም በንግሥት እንግሊዝ ግዛት ሳሉ ከፈቀዳቸው ከሌላ አገር ቢያልፉ አይከለከሉም ።

አስራሰባተኛ ።

የሐበሽ ንጉሥ ውል ይሰር በምንም ነገር በግዛተ ሐበሽ የእንግሊዝ ዜጎች በማንም ነውር በተከሰሱ ጊዜ በእንግሊዝ ንግሥት ኵንስል ይዳኙ ወይ በሌላ ሹም የእንግሊዝ ንጉሥ በዚያ የሾመው በማንም ነገር ጠብ ቢነሻ ምጉትም በእንግሊዝ ዜጎች ቢነሻ ወይም በእንግሊዝ ዜጎችና በሐበሻ ንጉሥ ዜጎች ማኸል ወይም በእንግሊዝ ዜጎችና በሌላ አገር ዜጎች ማኸል ቢነሳ በንጉሠ ሐበሽ ግዛት የሐበሽ ንጉሥ ኵንሰል ወይ ሌላ በዚያ የተሾመው ይሰማና ይዳኝ ማንም ማን ቢሆን ከሐበሽ ሹማምንቶች ሳይናገሩበት ሳይገቡበት ሳያስቸግሩት ምጉት ሲጀምር ወይም ሲማጎት ወይ ሲጨርስ ።

አስራስምንተኛ ።

የእንግሊዝ ዜጋ በሐበሻ ግዛት የሞተ እንደሆን የእንግሊዝ ኵንሰል ወይም ወኪላቸው የሞተውን ሰው ወረቀቱን ገንዘቡን ይቀበላሉ ብድር ቢኖርባቸው ወራሽ ቢኖራቸው ባለዳ ቢኖርባቸው ወስዶ እንዲሰጣቸው የሐበሻ ሹማምንት ሳያስቸግርዋቸው ።

አስራዘጠነኛ ።

በመጨረሻው ውል ይደረግ ይህ ሁሉ በፊት የተናገርነው አለመፍረስ የዘለ ዓለም ወዳጅነት በሁለቱ ነገሥታቶች ማኸል ይቆማል ።

በዚህ ምስክር ይህ ውል ታተመ ካሁን ቀደም በተጠራ ባቶ ፕላውዱንና በሐበሽ ንጉሥ በጃቸው ።

በናውጋ በ፯ ሺሕ ከ፫፻፵፪ ዓመተ ዓለም በ፲፰፻፵ወ፪ ዓመተ ምህረት በዘመነ ማርቆስ በጥቅምት በ፳፫ኛ ቀን ተደረገ በእንግሊዝ ታሪክ በ፲፰፻፵ወ፱ እምልደተ ክርስቶስ በኖቨምበር በ፪ኛ ቀን የወዳጅነትና የንግድ ውል በታሪክ እንግሊዝ በኖቨምበር በሁለተኛው ቀን እንደ ሐበሽ ታሪክ በጥቅምት በ፳፫ተኛው ቀን የተደረገ በንግሥት እንግሊዝና በሐበሻ ንጉሥ መካከል ማስሯው በንግሥትም እንግሊዝ ማኅተም የታተመ ካቶ ፕላውድን ኮንሰል እንግሊዝ በሐበሽ የሐበሻ ንጉሥ ተቀብየአለሁ ብለዋል ። ለዚህም ምስክር የሐበሻ ንጉሥ ማኅተም ታትሟል ። ዛሬ በማርች በፊተኛው ቀን በዓመተ ምህረት ሺሕ ከ፱፻ከ፶፪ እንደ ሐበሻ ታሪክ በየካቲት በ፳፪ ቀን በዓመተ ምሕረት ሺሕ ከ፱፻ከ፵፬ ።